ስለ ኤስ ኣይ ኤም ሠራተኞች ወይም የውጪ አገር ሚስዮናውያን ጥቂት አንቀጾችን ብጨምር አስፈላጊ ይመስለኛል:: በ1930ዎቹና በ1950ዎቹ ውስጥ ብዙዎቹ የውጭ አገር ሚስዮናውያን ወንጌልን ለእያንዳንዱ ሰው የማዳረስ ራእይ ነበራቸው:: ስለዚህም ነው ይህንን ምዕራፍ በአቶ መሐሪ ታሪክ ላይ የጨመርኩት:: ብራዬን ፋርገር

# ኤስ ኣይ ኤም በጋሞ ጐፋ

## ምዕራፍ ዘጠኝ

በመካከለኛው ደጋማ የኢትዮጵያ ክፍል ለሚኖሩ ሰዎች ጋሞ ጐፋ እንደ መሬት መጨረሻ ሆኖ ይታያል:: በጣም የራቀ የዓለም ክፍልና የጥንት ሰዎች የሚኖሩበት አድርገው ይገምቱታል:: ጋሞ ጎፋ በአገሪቱ ወደ ኋላ ከቀሩትና ከተረሱት አካባቢዎች አንዱ ነው:: በዚያ የሚኖሩ ሰዎች ግብር ይከፍላሉ፣ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውም ተነግሯቸዋል:: የሥልጣኔ ጥቅም ግን በጆሮአቸው ከመስማት ያለፈ አልነበረም:: አካባቢው በእርሻ የበለጸገ፣ የማይለወጥና በበዝባዥ የመሬት ከበርቴዎች ዕድገቱ የተቀማ እና መንገድ አልባ ነበር::

በኢትዮጵያ ኤስ ኣይ ኤም ሥራውን የጀመረው በደቡባዊ ኢትዮጵያ ሦስት የሚስዮን ጣቢያዎችን በማቋቋም ነው:- በሲዳማ ጋርብቾ፣ በወላይታ ሶዶ እና በሐዲያ ላምቡዳ በሚባሉ አካባቢዎች ነበር:: በመጀመሪያዎቹ ሁለትና ሦስት ዓመታት በእነዚህ ቦታዎች መኖሪያ ቤቶችንና ክሊኒኮችን በመገንባት፣ በመንግሥት በኩልም መሟላት የሚገባቸውን ሁሉ እያሟሉ አሳለፉ:: የኤስ ኣይ ኤም ሠራተኞች በደቡባዊው የአገሪቱ ክፍል የመጀመሪያዎቹ የውጪ አገር ሚስዮናውያን ሲሆኑ፣ መንግሥትና የአካባቢው ሕዝብ ከእነርሱ ምን መጠበቅ እንዳለባቸው አያውቁም ነበር::

በመጨረሻም እነዚያ የውጪ አገር ሚስዮናውያን በጋሞ ጐፋ ክፍለ ሀገር ሁለት የሚስዮን ጣቢያ ሠርተዋል:: በብዙ መንገድ ሁለቱ ቦታዎች የሚመሳሰሉ ሲሆኑ፣ ሥራው ግን የተለያየ ነበር:: ሚስዮናውያኑ ወደዚያ አካባቢ በግልጽ የገቡበት ምክንያት በመንግሥት



ባለሥልጣኖች ስለተጋበዙ ነበር:: በቡልቂ ከመንግሥት ድጋፍ ሲያገኙ፣ በጨንቻ ደግሞ ተቃራኒ ነገር ነበር የገጠማቸው::

ጋሞ ለወላይታ የሚቀርብ ሲሆን፣ በአባያ ሐይቅ ዳር ብዙ ምርታማ የሆነ ለም መሬት ነበረው:: ነገር ግን ከጐፋ ይበልጥ በጋሞ ብዙ የአማራ የመሬት ከበርቴዎች የሚኖሩ ሲሆን፣ በገበሬዎቹ ላይ የሚያደርሱባቸው ጫና እና ቅጣት ግን እጅግ የከፋ ነበር:: በተፈጥሮአቸው ሚስዮናውያኑ ለሚያስተምሩት ትምህርት ፍላጐት ያላቸው አልነበሩም፣ ለማንበብና ለመፃፍ እንዲሁ ጉጉ አልነበሩም:: በማንኛውም መንገድ ግን ሰዎች ስለራሳቸው እንዲያስቡ ማስቻል ያስፈልጋል:: የሚስዮናውያኑ ተግባር በሁለቱም ቦታ ሕክምና መስጠት ሲሆን፣ በጊዜው አማሮች የነበሩት ሰዎች ወደ ሕክምና ቦታ እንዳይሄዱና ሕክምና እንዳያገኙ በብዙ መንገድ መሰናክል ይሆኑባቸው ነበር:: ሚስዮናውያኑ ለመጀመሪያ በደረሱ ጊዜ ከመንግሥት መሬት እስኪያገኙ ድረስ ለተወሰኑ ወራቶች በጨንቻ ከተማ ተነጥለው ተቀምጠው ነበር:: በአካባቢው እየተዘዋወሩም ወንጌልን ይሰብኩ ነበር:: ይሁን እንጂ ከአማራ የመሬት ከበርቴዎች ጠንካራ ተቃውሞ ገጥሟቸዋል:: በጐፋ የአውራጃ አስተዳዳሪው ሚስዮናውያንን በመደገፍ ትምህርት ቤት እንዲሠሩ ካደረጉ በኋላ፣ የገዛ ቤተሰቦቻቸውንና ዘመዶቻቸውን አስገብተው እንዲማሩ አድርገዋል:: ክሊኒኩም ብዙ ደንበኛ ሕሙማንን የሚያስተናግድ ሲሆን፣ ሚስዮናውያኑም ለመዘዋወር ነጻነት ነበራቸው:: በጋሞ ግን እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ አልነበረም::

የውጪ አገር ሚስዮናውያን በ1929 ዓ.ም ጣሊያን አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ሁለቱንም ቦታዎች ለቅቀው ሄዱ:: ሚስዮናውያኑ ትተው የሄዱት ሁሉም ነገር የተዘረፈባቸው ሲሆን፣ ቤቶቹም ፈራርሰዋል:: እነርሱ ግን በሰላም አዲስ አበባ ከደረሱ በኋላ የጣሊያን ወረራ እስኪያበቃ ድረስ ኢትዮጵያን ለቅቀው ወደ አገራቸው ሄደዋል::

በጋሞም ሆነ በጐፋ ሚስዮናውያኑ ወንጌልን መስክረው የክርስቲያኖችን ሕብረት አላፈሩም:: የጋሞ አካባቢ ሕዝብ በጊዜው ወንጌልን ስለመቀበላቸው የተዉት ማረጋገጫ አልነበረም:: በጐፋ ግን የተወሰኑ ምእመናንን ያጠመቁ ሲሆን፣ ከተጠመቁት መካከል ጥቂቶቹን አቶ መሐሪ በመጨረሻ ወደ ጐፋ በሄዱ ጊዜ ተገናኝተዋቸዋል:: እነዚያ በጐፋ የነበሩት ክርስቲያኖች የውጪ ሚስዮናውያን ከዚህ ከሄዱ በኋላ

አልተሰባሰቡም ወይንም ሰወላይታ ክርስቲያኖች ራሳቸውን አላስተዋወቁም ነበርና በጣሊያን ወረራ ዓመታት ሁሉም አልተገናኙም።

የውጪ አገር ሚስዮናውያን ከሶዶ የወጡት በ1930 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ነበር። ነገር ግን የተወሰኑ የወላይታ ክርስቲያኖች በአዲስ አበባ ከቀሩት የውጪ ሚስዮናውያን ጋር ግንኙነት ያደርጉ ነበር። ያ ግንኙነታቸው ጣሊያን በ1931 ዓ.ም ሚስዮናውያኑን ከኢትዮጵያ ጨርሶ እስኪያስወጣ ድረስ ቀጥሎ ነበር። አገሪቱ በጣሊያን ወረራ ሥር በነበረችበት ጊዜ ለሦስት ዓመት በወላይታ የወንጌል ስርጭቱ የቀጠለ ሲሆን፣ ቤተክርስቲያን በስፋት እየተመሠረተች ከጣሊያን ደጋፊ ሰዎችም ተቃውሞው እየበረታ ነበር። በደቡባዊ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሶዶ በወቅቱ ትልቁ ከተማ ነበር። እንዲሁም በደቡብ የጣሊያን አስተዳደር ማዕከላዊ ቦታ ነበር። ቁጫና ኦቾሎ በሚባሉ ቦታዎች የሚኖሩ ሰዎች ልዩ የበዓል ቀናቶቻቸውን በሶዶ እንዲያሳልፉ ይታበዙ ስለነበር፣ አማኞቹ ከወላይታ ክርስቲያኖች ጋር ይገናኙ የነበሩት በዓላቶቻቸውን ምክንያት እያደረጉ ሲሄዱ ብቻ ነበር።

በ1932 አካባቢ የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ ሥልጣኑ ከመመለሱ ቀደም ብሎ ከወላይታ ቤተ ክርስቲያን የወጡ ወንጌላውያን ወደ ወላይታ ድንበር ዘልቀው ወንጌልን ይሰብኩ ነበር። ሁለት ትናንሽ ማኅበራት በጋሞ ሁለት ቦታዎች ማለትም በኦቾሎና በማርገሬታ ሐይቅ ዳርቻ ተመሠረቱ። በተጨማሪም በ1932-1934 ዓ.ም ጥቂት ሰዎች በቁጫ ወንጌልን ሰምተው ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ተቀብለዋል።

በ1933 ዓ.ም ላውሪ ዴቪስን የሚባሉ ሚስዮናዊ ቀደም ሲል በቡልቂ ይሠሩ የነበሩ በኋላም በጣሊያን ወረራ ጊዜ በወላይታ ይሠሩ ነበር። ወደ አገራቸው ከሄዱ በኋላ ከብሪታንያ ጦር ጋር ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው መጡ። በጥቂት ሳምንቶች ውስጥ ከወላይታ ክርስቲያኖች ጋር ግንኙነት ፈጥረው ቤተ ክርስቲያን በወላይታ አካባቢ እየተራባች መሆኗን ሰሙ። እነዚያን ክርስቲያኖች ዳግመኛ ወደ ወላይታ ሄዶ ለመጎብኘት ሁለት ዓመት ያህል ወስዶባቸዋል። ከዚያም ከ18 ወር በኋላ የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮናውያን በአዲስ አበባ ሲጠባበቁ ቆይተው ከመንግሥት ፍቃድ በማግኘት በደቡብ ሄደው ለመስፈርና ለመሥራት ችለዋል።



በእነዚያ በአራት ዓመታት ውስጥ ማለትም ከ1933 እስከ 1936 ዓ.ም ውስጥ የጣሊያን ወራሪ ኃይል በኢትዮጵያ መንግሥት ሲሸነፍ የወላይታ ቤተ ክርስቲያን ሥራ በጣም አድጓል። በወላይታ ውስጥና ከድንበር አልፎ የአካባቢው ሕዝብና ወንጌላውያኑ እየተዘዋወሩ ለመስበክና ለማስተማር ችለዋል።

## *ወደ ምዕራፍ አሥር መግቢያ*

*አቶ መሐሪ ደጋግመው እንደተናገሩት ከባሊያን ወረራ በኋላ በምንም ዓይነት መንገድ በጐፋ የመጀመሪያ ወንጌላዊ አልሆኑም። ታሪክ እንደሚገልጸው አንድ ሰው የበላይነትን በሚያሳይበት ጊዜ ቡድኑ አደጋ ላይ እንዲወድቅ ያደርጋል። አቶ መሐሪ ሌሎችን በማስቀደም ይታወቃሉ። በ1933 ዓ.ም አካባቢ በወላይታ ውስጥ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በሰፊው መስራጨትና ማደግ ጀምራለች። የወላይታ ወንጌላውያንም ለተወሰኑ ዓመታት ወደ ጐፋ እየሄዱ ማስተማር ጀምረዋል። ይህም አቶ መሐሪ ወደ ጐፋ ለመሄድ የእግዚአብሔርን ጥሪ ከመቀበላቸው በፊት ነበር።*

*የእነዚያ ወንጌላውያን አስደናቂው ነገር እውነትን መመልከት የሚቻለው መዋቅር የሌለውና የአስተዳደሩ የበላይ ተመልካችነት የጐደለው ቢሆንም፣ ብዙዎቹ ከነቤተሰቦቻቸው የተቀናጀ አብሮ የመሥራት እውነታ ግን ነበረባቸው። አቶ መሐሪ ከእሥራኤል ጋር የነበራቸው ልምድ ለየት ያለ ነው።*

*ወንጌላውያን ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ጥሪ ለማረጋገጥ ጠንቃቃ ናቸው። እግዚአብሔር የሚጠራቸውን ሰዎች ለማወቅ ጽንሰ ሃሳብን አልተማሩም። ነገር ግን እግዚአብሔር እስከጠራቸው ድረስ ወደ መራቸው ቦታ ይሄዳሉ። ይህም ማለት ለጥሪው ጥቂት ሰዎች ማረጋገጫ አግኝተዋል። ይህንንም በስብከታቸው ለማረጋገጥ ዝግጁዎች ነበሩ። ቀስ በቀስ ከብዙ ዓመታት በኋላ ጥቂት ቁጥር ያላቸው ሰዎች በጐፋ ባልተጠበቀ ሰዓት ቃሉን ሰምተው ተቀብለዋል። ይሁን እንጂ መልእክቱን «እሺ» ብለው የተቀበሉ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎች አልነበሩም።*

*ለወንጌላውያን እግዚአብሔር የጀመረውን ሥራ ይተዉ ዘንድ ምንም ተቃውሞ ምክንያት አይሆንባቸውም። ምን ጊዜም ለሚመጣባቸው ስደት መዘጋጀት እንደሚገባቸው መጽሐፍ ቅዱሶቻቸውን በማንበብ ተገንዝበዋል።*

*አቶ መሐሪ የአገልግሎታቸውን ክስተት በአጠቃላይ በዝርዝር ይመድባሉ። ምናልባት ይህ አንባቢውን ያደናግር ይሆናል ያም ማስወገድ የማይቻል የባህል መሰያ ነው።*



# ቁጫን መሰናበት

## ምዕራፍ አሥር

በ1940 ዓ.ም ከፊታውራሪ ሴሎ ልጅ ጋር ለአንድ ሳምንት ጐፋን በጐበኘሁ ጊዜ ጥቂት ፊደሎችን ይዤ ሄጃለሁ። የፊደል መጽሐፎቹ ከፊት ለፊታቸው የኢትዮጵያ ባንዲራ ምስል ነበራቸውና የባንዲራ ፊደል እያልን እንጠራቸው ነበር። በጊዜው ብዙ ሰዎች ማንበብና መጻፍ ለመማር ይፈልጉ ስለነበር ብዙ ፊደሎችን ያን ጊዜ ለመሸጥ ችለናል።

በ1941 ዓ.ም የተወሰኑ የወላይታ ወንጌላውያን ወደ ጐፋ ሲሄዱ እግረ መንገዳቸውን ወደ ቁጫ መጡ። ሁለቱ ወንጌላውያን ማዴቦ ቦቂ እና እሥራኤል ይባላሉ፣ ሁለቱም ለጥቂት ቀናት ያህል በእኛ አካባቢ ቆይተዋል። ሁለቱም ለጉዞአቸው የሚሆን ገንዘብ ተሰጥቷቸው ነበርና በገንዘቡ ምክንያት በመካከላቸው በተፈጠረው ጠብ የተነሣ ማዴቦ ወደ ወላይታ ተመለሰ። ሌሎች ሁለት ወንጌላውያን የነበሩት አንጃሎ ዱባና እና ማጃ ማርቆ ሲሆኑ፣ እነርሱም ከቁጫ ማኅበር የወጡ ነገር ግን በገንዘብ በወላይታ ቤተ ክርስቲያን የሚደገፉ ነበሩ። ከሁለቱ አንዳቸውም እንኳን በጐፋ ለረዥም ጊዜ አልቆዩም።

ከእነዚህ ወንጌላውያን ጋር እኔ ወደ ጐፋ ለመሄድ ፈልጌ ነበር። ነገር ግን ታናሽ እኅቴ ታገባ ስለነበር ለሚያስፈልገው ዝግጅት ሁሉ መገኘት ነበረብኝ።

ስለዚህ፣ «እናንተ አስቀድማችሁ ወደ ጐፋ ሂዱና ስለ ሁኔታው ስትመለሱ ንገሩኝ» አልኳቸው። መመለሳቸውን በጉጉት እጠብቅ ስለነበረ የሠርጉን ሥነ ሥርዓት በሚገባ አልተከታተልኩም ነበር።

ማዴቦና እሥራኤል ወደ ወላይታ በተመለሱ ጊዜ በገንዘብ ምክንያት የነበረባቸውን ጠብ አስወግደው ተስማምተው በመጨረሻም በወንጌላዊነት ወደ ጐፋ ለመሄድ ፈለጉ። በሁለተኛው ጉዞአቸው በስፋት እስከ ዛላ ድረስ ይዘዋወሩ ነበርና በዚያ አጋጣሚ እሥራኤል በኃይለኛ ተቅማጥ ስለተያዘ እጅግ በጣም ታሞ ነበርና ወደ ወላይታ መመለስ ነበረበት። ከእሥራኤል ጋር በጐፋ ወንጌልን ስለመስበክ በሰፊው ተወያየን። እዚያ ለመሄድ ልቤ በጣም ይነሣሣ እንጂ፣ ጊዜው ግን አመቺ አልሆነልኝም። ነገር ግን በቅርቡ ወንጌላዊ ሆኜ ወደ ጐፋ

እንደምሄድ እርግጠኛ ነበርኩኝ። ለጊዜው ግን የቋሚ ማኅበር በጥሩ ሁኔታ ተይዞ እንደሆነ የመመልከት ኃላፊነትም ነበረብኝ።

## ከእሥራኤል ጋር የመጀመሪያ ጉዞ

እሥራኤል ከሕመሙ ካገገመ በኋላ እንደገና ወደ ጐፋ ለመሄድ ወሰነ። በዚያን ጊዜ ከእኛ ዘንድ ቆይቶ ነበር። ከእርሱ በመገናኘቴ በጣም ደስ ብሎኛል። ወደ ጐፋ ከእርሱ ጋር ሄጄ ለመጐብኘት ጊዜው አሁን ነው አልኩኝ። በእርግጥ ወደ ጐፋ የምንደርስ አልመሰለኝም ነበር። የሚታወቀኝ ነገር ግን ይህ በሕይወቴ ውስጥ አሳዛኝ ጉዞ እንደነበር ነው። ምክንያቱም ከክርስቲያን ወንድም ጋር ተኳርፎ አብሮ መሄድን የመሰለ አሳዛኝ ነገር የለም።

እኔና እሥራኤል ወደ ጐፋ አብረን በተጓዝን ጊዜ የአማርኛ ፊደል መማሪያ መጽሐፍ ይዤ ነበር። አንዳንድ ወንጌላውያን በወቅቱ በጣም ውድ ስለነበረ ጨው ይዘው ይሄዱ ነበር። በመንገድ ላይ ለሚያገኙ አቸው ሰዎችና በየስፈሩ በአነስተኛ ገበያ ሁሉ ጨው እየሸጡ ሰዎችን የመገናኘት አጋጣሚ እያገኙ ወንጌልን ይሰብኩ ነበር። እኔም ፊደሉን ይዤ እሄድ የነበረው ሰዎችን ፊደል ለማስተማር እንድችል ነበር። ያ ዘዴ ሰዎችን በፊደል ሰበብ በመሳብ ወንጌልን ለመስበክ ዓይነተኛ ብልሃትም ነበር።

በዚህ ጉዞአችን ወቅት ሄደን ያረፍነው በአንድ ግብር ተቀባይ በሆኑ በባላምባራስ ኮራ ቤት ነበር። ቤታቸው የደረስነው አመሻሹ ላይ ነበርና ወደ ቤታቸው እንድንገባ ጋበዙን። እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት እራት እስኪቀርብ ድረስ በብዙ የተለያዩ ነገሮች ዙሪያ ተወያየን። ምግቡ በፊታችን ባለው ጠረጴዛ ላይ እንደቀረበ፣ «እኔ ልማድ አለኝ። ምን ላድርግ?» ብዬ ባላምባራስን ጠየቅኋቸው።

«ምንድን ነው ልማድህ?» አሉኝ።

«ከመመገቤ በፊት አስቀድሜ እጸልያለሁ። ጥሩ ነው። እኛም እግዚአብሔርን ማመስገን አለብን። በል አመስግንና እንብላ» አሉኝ።

ከጸለይኩኝ በኋላ፣ ከብዙ ዓመት በፊት ወንጌልን ከሚስተር ኦህማን እንደ ሰሙ ነገሩኝ። ትምህርቱ ጥሩ እንደነበር ገልጸው መጥቼ በአካባቢያቸው ወንጌልን እንድሰብክ ጋበዙኝ።



## የገንዘብ ችግር

በዚህ ጉዞ ላይ ጓደኛዬ ከጅምሩም አላመነኝም ነበርና ጉዞአችንን ጀምረን ብዙ ሳንርቅ እሥራኤል የወባ በሽታው ተነሣበትና ምንም ነገር መያዝ አልችልም በማለቱ የያዝነውን ምግባችንን እኔ ብቻዬን ለመሸከም ተገደድኩ። በእግራችን ከቋሚ እስከ ዛላ ድረስ ተጉዘን ሦስት ቀን ቆየን። ከዚያም መንገዳችንን ከቆላ ወደ ደጋ በማድረግ ወደ ቡልቂ ከተማ ለማቅናት ወሰንን። በመጨረሻም ቡልቂ ያላ ወደሚባል ቦታ ደረስንና በአቶ ደልቦ ቤት አረፍን። እርሱም በ1922 ዓ.ም የውጪ አገር ሚስዮናውያን ሄደው ይሰብኩ በነበረ ጊዜ እምነቱን የተቀበለ ሰው ነበር። የሚያበረታታውን ሰው ከማጣቱ የተነሣ በክርስትና ሕይወቱ ያሳየው ዕድገት አልነበረም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ በነበሩበት ወቅት እኛ ስንደርስላቸው እርሱና ባለቤቱ በጣም ደስ አላቸው። ቤታቸውን ማረፊያችን በማድረግ በአካባቢው እየተዘዋወርን በገጠሩ ወንጌልን ለመስበክ እንቅስቃሴ ጀመርን።

እሥራኤል ከወላይታ በተነሣ ጊዜ በኪሱ ሠላሳ ብር ይዞ ነበር። ሁሉንም ብር ይዞ ወደ ጐፋ ከመጓዝ ይልቅ ሃያ ሰባት ብር ከባለቤቱ ዘንድ ትቶ በኪሱ ሦስት ብር ብቻ ይዞ ለመሄድና ከጐፋም ስንመለስ ሃያ ሰባቱን ብር ከባለቤቱ ተቀብሎ ወደ ወላይታ ለመሄድ ወሰነ።

ብዙ መንገድ ርቀን ሳንሄድ፣ እሥራኤል፣ «ይህንን ሦስት ብር በአንተ ኪስ ያዝልኝ» አለኝ። ጥያቄው ሊገባኝ የማይችል እንቆቅልሽ ቢሆንብኝም፣ ሦስቱን ብር ተቀበልኩትና ከውስጥ ሸሚዜ በመርፌ ቁልፍ አጣብቄ ቆልፌ ያዝኩለት። በኋላ እንደተረዳሁት ግን የሰጠሁህ አራት ብር ነው ብሎ አንድ ብር ትርፍ ሊያስከፍለኝ አስቦ ኖሯል። ገንዘቡን በጉዞአችን ላይ ፍጹም አስፈላጊ ለሆነ ነገር ብቻ እናወጣ ስለነበር አንድ ብር በጊዜው ለአሥራ አምስት ቀን ይበቃን ነበር።

ይሁን እንጂ እሥራኤል አራት ብር በኪሱ ይዞ ከባለቤቱ ዘንድ ሃያ ስድስት ብር እንዳስቀመጠ በአእምሮው አስቧል። ስለዚህ የሰጠሁህ አራት ብር ነው አንድ ብር ወስደህብኛል እያለ ይሟገተኝ ነበር። እኔም መከራከርህን ተውና ወደ ቤት ስንመለስ ከባለቤቱ ዘንድ ስንት ብር እንዳስቀመጥክ አረጋግጥ እያልኩ እወተውት ጀመር። ነገር ግን አልሰማኝም፣ እንደ ሠረቅሁት አድርጎ ይሰድበኝ ነበር።

ከቦታ ወደ ቦታ የምንዘዋወር እንደ መሆናችን ብዙውን ጊዜ ምግብ ገዝተን እንይዛለን። ምክንያቱም የተወሰነ ማደሪያ ቦታ ስለሌለንና

ሲመሽብን በምናድርበት ምግብ ልናገኝ ስለማንችል ነው። ብዙ ሰዎች እንግዶችን ስለሚፈሩ /ስለማያምኑ/ ሌሊቱን ተቀብለው ላለማሳደር ምክንያት ይፈጥሩ ነበር። ይህንን በመፍራታችን ሁልጊዜ በከረጢታችን ባቄላ ገዝተን እንይዝና በምሽቱ በምናርፍበት ቦታ ለእራታችን እየቆላን እንመገብ ነበር። በእነዚያ ጊዜያቶች ውኃ ስንፈልግ በአጠገባችን ከምናገኛቸው ምንጮች እየሄድን እንጠጣ ነበር። ለጥቂት ቀናት በዚያ ሁኔታ ስንጓዝ ቆይተን ካሪዛ ወደሚባለው መንደር መድረሳችንን ስናውቅ ልዩ ደስታ ተሰማን።

በዚህ ቦታ ነበር ዓለሙ ከልሌ የሚባለውን ሰው የተገናኘነው። እዚያ ቦታ እንደ ደረስን እሥራኤል ስብከቱን ጀመረ። ዓለሙ ተነሣና፣ «ይህ መልእክትማ ሚስተር አህማን ከሰበከው ጋር ተመሳሳይ ነው። ለመሆኑ ምሽቱን የት ነው የምታድሩት?» አለ።

ማደሪያ እንደሌለን ሲረዳ ወደ እርሱ ቤት ገብተን እንድናድር ጋበዘን። በቤቱ ለእያንዳንዳችን ሁለት ቅል ወተት ከእራት ጋር ተሰጥቶን ጠጣን። ወደ መኝታችን ከመሄዳችን በፊት በቤቱ ውስጥ ያለው አገልጋዩ እግሮቻችንን እንዲያጥበን አደረጉ።

«ተመልሳችሁ እዚህ አካባቢ ሥሩ። የምታርሱትንም መሬት እሰጣችኋለሁ» ብሎ ቃል ገባልን።

ያም ካሪዛ በሚባለው መንደር ውስጥ ነበር። ከዚያ ቦታ ዘልቀን ዛንጋ ወደሚባለው ቦታ ተሻገርን። ያ ቦታም ከካሪዛ የሃያ ደቂቃ ያህል በእግር የሚያስኬድ ቦታ ነው። በዛንጋም ዳሲቦ ዳሎ የሚባል ሰው በመጀመሪያ ስብከታችን ጌታን ሲቀበል ደስታችን ወሰን አልነበረውም።

ወንጌላውያንን በማግኘታቸው ሰዎች ምን ያህል ደስተኞች እንደሆኑ ስንገነዘብ ወደ ቁጫ ተመልሰን ምን ዓይነት ቀጣይ እርምጃ እንደምንወስድ ለማቀድ ወሰንን።

የእሥራኤል ባህርይ የባሰ እየተበላሸ ሄደ። አንድ ብር ሰርቀኸኛል ብሎ ቁጣው የማይበርድ ሆነ። ወደ ቁጫ በተመለስን ጊዜ በቀጥታ ወደ እኔ ቤት እንድንሄድና ከባለቤቴ ዘንድ የተወውን ገንዘብ እንዲቆጥር ነገርኩት። እንቢ አለኝ። ወደ ባለቤቴ ለገንዘቡ የሄደው ከአያሌ ቀን በኋላ ነበር። ከባለቤቴ ሃያ ሰባት ብር ቢቀበልም እኔ የጐደለውን ሞልቼ እንደ ሰጧት ቆጠረ እንጂ አላመነም ነበር።



ይህንን አለመግባባት የፈጠረው ሰይጣን ነው። ምክንያቱም በጐፋ እየተካሄደ ያለውን ሥራ ለማደናቀፍ ነበርና ዳግመኛ ከእሥራኤል ጋር የትም ቦታ ላለመሄድ ወሰንኩ።

እኔም እንደ ሥራ ባልደረባነቴ እንዲህ አልኩት፣ «እግዚአብሔር ወዴት እንደሚመራህና እኔንም ወዴት እንደሚመራኝ አላውቅም። በአንድ ነገር ግን እርግጠኛ ነኝ፣ አብረን ልንሠራ አንችልም። አንተ በመንገድህ ሂድ፣ እግዚአብሔር ይባርክህ» አልኩት።

ይህ ልምምድ የሚያስጨንቀኝ ቢሆንም ስብከቴን ላለመቀጠል ተስፋ አልቆረጥኩም። ለተወሰኑ ጊዜያቶች በጐፋ አካባቢ እየገባሁ እሰብክ ነበር። ነገር ግን በማንኛውም ቦታ ረዘም ያለ ጊዜ ቆይቼ ቤተ ክርስቲያን አልመሠረትኩም።

## ዮሐንስና አቶ መሐሪ አብረው ሲሠሩ

በዚህን ጊዜ ዮሐንስ ዳራታ የሚባል ወንጌላዊ ከወላይታ ከእሥራኤል ጋር ወደ ጐፋ መጣ። ካሪዛ በሚባለው ቦታ አርፈው ሳለ ዮሐንስ አቶ ዓለሙን በወንጌል ስብከት ወደ ጌታ መለሰው። (አቶ ዓለሙ ከእኔ ጋር አዲስ አበባ ሄዶ የነበረው አይደለም)። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ዓለሙና ባለቤቱ ተጠመቁ፣ በጐፋ የመጀመሪያው ጸሎት ቤት የተሠራውም በካሪዛ ነበር።

እሥራኤል በጐፋ ከፍተኛ የሆነ ሥራ ለጌታ ከመሥራቱም በላይ፣ በብዙ በተለያዩ ቦታዎች ወንጌልን ሰብኳል፣ ብዙ ሰዎችን ወደ ጌታ ከመምራቱም በላይ አያሌዎችን የማጥመቅ አጋጣሚ አግኝቷል። አጋጣሚ ሆነና ዮሐንስና እሥራኤል ረዥምና መራራ ወደሆነ አለመግባባት ላይ ስለደረሱ እሥራኤል ወደ ወላይታ ለመመለስ ወሰነ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ትምባሆ ማጨስና ሌሎች ክርስቲያኖች የማይፈጽሟቸውን ድርጊቶች መፈጸሙ ሲገርመኝ እንዲያውም ከጥቂት ጊዜ በኋላ የአዕምሮ መታወክ እንደ ደረሰበት ሰው መሆን ጀመረ። የዚህ ሰው አሟሟቱም የገጠሩን ሕዝብ ሁሉ ያስደነቀ ነበር። በ1943 ዓ.ም አካባቢ አንድ ቀን ወደ ገበያ ሄደ፣ እዚያም ከመጠን በላይ የአልኮል መጠጥ በመጠጣት በመንገድ ጥግ ወድቆ በዚያው አንቀላፋ። ማንም አላየውም ነበርና በምሽቱ ጅቦች ወጥተው ተቀራመቱት።

እሥራኤል ከጐፋ ወደ ወላይታ ከተመለሰ በኋላ ዮሐንስ ወደ እሥር ቤት ገባ። በመጀመሪያ ዮሐንስና ዓለሙ ሁለቱም በሎቲ ወረዳ

ታሥረው ነበር:: በኋላም ወደ ቡልቂ ከተማ ተወስደዋል:: ዓለሙ ከተፈታ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ሄዶ ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋር አልተባበርም ብሎ ለብቻ ወንጌልን መስበክ ወንጀል አይደለም የሚል ወረቀት ተሰጥቶት ተመለሰ:: ዮሐንስ ደግሞ ለባት ወር ታሥሮ ከተፈታ በኋላ በጎፋ ቆይቶ ለብቻው መሥራት መልካም እንዳልሆነ ተገነዘበና እባክህ ከእኔ ጋር አብረን በጐፋ ወንጌልን እንሰብካለን ብሎ መልእክት ላከብኝ::

የመጨረሻ ውሳኔዬን ከመወሰኔ በፊት አንድ ጊዜ ወደ ጐፋ ለመሄድና በእውነት ጌታ እዚያ እንድሠራ ፈልጐኝ እንደሆነ ለማረጋገጥ ስለፈለግሁ ከዮሐንስም ጋር እየተዘዋወርኩ ጥቂት ሳምንቶች አሳለፍኩ:: በብዙ ቦታዎችም አብረን እየሄድን ወንጌልን ሰበክን:: ከዚህም በኋላ ምንም ዓይነት ችግር ከፊቴ ቢጋረጥብኝ እንኳን ይህ ቦታ እግዚአብሔር እንዳገለግለው የወሰነልኝ ቦታ መሆኑን ለማረጋገጥ ቻልኩ::

ከዚህ ጉብኝቴ በኋላም ወደ ቁጫ ተመለስኩኝ:: ከዚያም የወላይታን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና የሥራ አመራር ቦርድን ወደ ጐፋ ለመሄድ ፈቃድ እንዲሰጡኝ ለመጠየቅ ወደ ወላይታ ሄድኩኝ:: እነርሱም የሙሉ ጊዜ ወንጌላዊ እንድሆን ፈቀዱልኝ:: ደግሞም የቁጫን ማኅበር የሚንከባከብ ሰው እንደሚመድቡና እንደሚረዱ ቃል ገቡልኝ:: በወንጌል አገልግሎት አንድ ሆነው ከጐኔ እንደሚቆሙ ቢያረጋገጡልኝም ያ ማለት ግን ደመወዝ ይከፍሉኛል ማለት አይደለም:: እነርሱ ያረጋገጡልኝ ወደ ጐፋ የምሄደው ከእነርሱ ተልኬ መሆኑንና የሽማግሌዎች ቦርድ ገንዘብ ሲያገኝ ብቻ ደመወዝ ሊከፍለኝ እንደሚችል ነው:: አንዳንድ ጊዜ ምንም ገንዘብ ሳንቀበል ለእያሌ ወራት እንሠራ ነበር:: ቦርዱም የተወሰነ የወር ደመወዝ ይሰጠናል ብለን ምንም ትኩረት አንሰጥም ነበር:: እንዲሁም ቦርዱ በየወሩ ሳያቋርጥ ደመወዝ ለመላክ አይገደድም::

ያኔ እኔ የ28 ዓመት ወጣት ነበርኩኝ፣ ወደ ቀለም ት/ቤት ወይም ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት አልገባሁም ነበር:: የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስን ግን ማንበብ ችዬ ነበር:: የምሰብከውን መልእክት አውቅ ነበር:: እስከዚህ ያደረሰኝ ጌታ በሕይወት እንደሚያቆየኝና እስከ መጨረሻም እንደማይለየኝ እርግጠኛ ነኝ:: ከሶዶ ወደ ቁጫ ስመለስ ልቤ በደስታ ተሞልቶ ስለተነሣሣ አሁን ቤተሰቦቼን ወደ ጐፋ ለመውሰድ ዕቅድ ማውጣት ጀመርኩ::



## ወደ ምዕራፍ አሥራ አንድ መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አቶ መሐሪ ከአንዱ የኢትዮጵያ ክፍል ወደ ሌላኛው ክፍል ለመዛወር ለማንም ወንጌላዊና ለቤተሰቡ በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ ይናገራሉ:: ነገር ግን አቶ መሐሪ ከአንድ ባህል ወደ ሌላ ባህል መዛወር የበለጠ እንደሚከብድ ከሙያቸው ልምድ አካብተዋል:: የጐፋ ቋንቋና የገቢ ምንጭ ከቁጫ አካባቢ ተመሳሳይ ቢሆንም፣ አቶ መሐሪ ግን ሦስት የግል ተግዳሮቶች ነበሯቸው:: ይኸውም ከሰፊው የቤተሰብ ድጋፍ መዋቅር መለየት፣ አዳዲስ ወዳጆችን የማፍራት ፍላጐትና እርሻቸውን ለመጀመር መሬት የማግኘ ት አስፈላጊነት ሲሆኑ፣ የገንዘብ ጉዳይ እንደዛሬው አሳሳቢ አልነበረም::

በአዲስ አካባቢ ወንጌልን መስበክ ማለት ከባህል ጋር ፊት ለፊት መጋፈጥ ሲሆን፣ አንድ ሰው ከጨለማ ወደ ብርሃን በሚያልፍበት ጊዜ በጨለማ ውስጥ ከቀሩት ጋር ግጭት እንደሚፈጠር ግልጽ ነው:: ከዚህም ባሻገር ባህላዊ አለመረዳት የነበረ ሲሆን፣ አቶ መሐሪም ከብዙዎች ወንጌላውያን እንደ አንዱ ሆነው ይህንን ተለማምደዋል::

ከባሕል ጋር ፊት ለፊት መጋፈጥ ወይም ባህልን መቃወም የማይቀር ነበር:: ነገር ግን ባህልን አለማወቅ ለሌሎች ስሜት ግድ ማጣት ማለት አይደለም:: አቶ መሐሪና ሌሎች ወንጌላውያን የዚያን የተከለከለውን ነገር ትርጉም ያውቁ ነበር:: ከቀን ወደ ቀን የተለያዩና የተከለከሉ ነገሮች ከእነርሱ ጋር ሊያያዝ የሚችለውን ያውቁ ነበር:: ጥያቄዎችን ለመጠየቅ በሚገባ የሚቻል መሆኑንም ደግሞ ያውቁ ነበር::

በእርግጥ የሰዎችን ባህል የሚገልጽ ጥናት አልወሰዱም ወይም አልተማሩም:: በየሄዱበት ቦታ ግን ወንጌልን ከየባሕሉ ጋር አዋህደው በሚገባ ለማስተላለፍ ችለዋል::

# በጐፋ ውስጥ

## ምዕራፍ አሥራ አንድ

በዚህን ጊዜ የጓሮ አትክልት ቦታዬን አስፍቼ እርሻዬም መልካም ፍሬ እየሰጠኝ ቅጠላ ቅጠሎችም ደርሰውልኝ ተግቼ በመሥራት ያፈራሁትን አትክልት ስመለከት እደነቅ ነበር:: ምን ላድርግ? ወደ ውሳኔዬ ከመምጣቴ አስቀድሜ ሰወር ብዬ ለመጸለይ ወሰንኩ:: ይህን ሁሉ በመተው በባይተዋር ሕዝብ መካከል ሌላ ሥራ መጀመሩን አላስመለከተኝም::

ከምጸልይብት ቦታ ተመለስኩና ወደ ባለቤቴ ዘወር ብዬ፣ «በላይነሽ» አልኳት፣ «ወደ ጐፋ ሄጀ ወንጌልን ለመስበክ ወስኛለሁ:: ምን እናድርግ?» አልኳት::

እዚያ ብንሄድ ኑሮው ለእርስዋ ቀላል አለመሆኑን ብትረዳም አብራኝ ለመሄድ ፈቃደኛ መሆኗን ገለጸችልኝ:: እግዚአብሔር በልቧ ይህንን ለውጥ እንድታመጣ እርሱ ሠርቷልና::

ታናሽ ወንድሜ ዳንኤልም ውይይታችንን ይሰማ ስለነበር፣ «ሁለታችሁም የምትሄዱ ከሆነ፣ እኔም አብሬአችሁ እሄዳለሁ» ብሎ ቁርጥ ውሳኔውን ሲነግረን፣ እኅቴም በበኩሏ፣ «እኔን ለብቻዬ እዚህ ትታችሁኝ ወደ ጐፋ የምትሄዱበት ምንም ምክንያት አይኖርም:: እዚያ ሄጀ የምችለውን ሁሉ እሠራለሁ:: ቤት መጥረግ፣ ውኃ መቅዳትና ልጆችን መጠበቅ እችላለሁ ስለዚህ ሁላችንም ተያይዘን ብንሄድ እኔም በጣም ደስ ይለኛል::» በማለት የማያወላውል ቆራጥ አቋሟን አከለች::

የእኅቴ ባል እርሷን ፈትቶ ሌላ ሚስት ያገባ ስለሆነ ዳግመኛ እርሷን ሊያገባት አይፈልግም:: ባሏ ልጅ ለመውለድ የማትችል መሆኗን ሲረዳ ወደ ጠንቋይ በመሄድ አማክሮ ጠንቋዩም ሚስቱ ብዙ ሳትቆይ እንደምትሞት ይነግረውና ከመሞቷ በፊት ፈጥነህ ወደ ቤተሰቦቿ መልሳት ብሎ ስለመከረው ወዲያው ፈታትና ፈጥኖ ሌላ ሚስት ሲያገባ፣ እኅቴንም ከእርሱ የተገለለች አደረጋት::

እኛ ከጠበቅነው በላይ ጐረቤታችን የበለጠ ነገሩን የተረዱ በመሆኑ፣ «ወቅቱ የመከር ጊዜ ነው:: ወንድምህና እኅትህ እዚህ ቆይተው እህሉን ከሰበሰቡ በኋላ ወደ አንተ ወደ ጐፋ ለምን አይሄዱም?» የሚል ጥያቄ አቀረቡልኝ::



«ወደ ጐፋ የምንሄድበት ጊዜ አሁን ስለሆነ እዚሁ ለመቅረት የሚፈልግ የለም አልኳቸው:: እግዚአብሔር ግን የሚያስፈልገንን ሁሉ ሊሰጠን እንደሚችል እናውቅ ነበርና በእግዚአብሔር ብቻ ታምነን ወደ ጐፋ ለመሄድ ስንነሣ እርሱ እንደማይጥለንም እንተማመን ነበር::

## ቤተሰቡ ወደ ጐፋ ተንቀሳቀሰ

የጐፋ ጉዞ አስቸጋሪ ነበር:: ወደ ማዜ ወንዝ ከመድረሳችን በፊት አምስት ቀን ሙሉ ተጓዝን:: ወንዙን እንደ ተሻገርን ኃይለኛ ዝናብ መዝነብ ስለ ጀመረ ዝናቡ እስኪያባራልን ድረስ ለመጠለል ቀድመን ወዳየነው ቤት ስናመራ ልብሳችንን አድርቀን ሙቀት ለማግኘት ተስፋ ነበረን:: ትንሽ የምናውቀው ነገር ቢኖር ወደ ቤት በገባን ጊዜ ከአሮጌው ባህላችን ፍርሃትና ከንቱ አምልኮ የተነሣ መጥፎ ሁኔታ አስከተለብን::

በአገራችን ሕፃናት እስከ ሁለት ዓመት ዕድሜ ወይም ከዚያ በላይ እስኪሆናቸው ድረስ ጡት ይጠባሉ:: ለዚህም ነው ልጃችን ዕድሜው ከሁለት ዓመት ቢበልጥም እየጠባ የነበረው:: ወደዚያ ቤት በገባን ጊዜ ልብሶቻችን ረጥበው ከመበስበሳቸውም በላይ ከደጋማው አየር የተነሣ ብርድ ያንዘፈዝፈን ነበር:: ባለቤቴ የት እንዳለች ሳታስብ ሕፃኑን ልጃችንን ማቴዎስን በጭኗ አስቀምጣ ትመግበው (ታጠባው) ጀመር::

በጋሞ ጐፋ የሚኖሩ ሰዎችና ሌሎች ጐሳዎችም ጭምር በዓለም ውስጥ ቤተሰብን በአንድነት የሚያስተሳስርና የሚያድን ቅዱስ ኃይል እንዳለ በጋራ ያምኑ ነበር:: ይህ ኃይል በሕይወት ያሉትንና የሞቱትን ቤተሰቦች በደም የሚያስተሳስር ሲሆን፣ ለውጪዎቹ ሰዎች ብዙ እንደዚህ ዓይነቶቹ ተግባሮችና እምነቶች የቤተሰብ ኅብረትን ያድናል ከሚል ሃሳብ የመነጨ ትርጉም የለሽ ይሆንባቸዋል:: ቤተሰብን የሚጐዳ የሚመስላቸውን ነገር ሁሉ ሰዎች ይፈሩ ነበር:: በተለይም ወደ ቤት ለሚገቡት ሰዎች የሰይጣንን መንፈስ ለማጥፋትና መጥፎ ዕድል የሚሉት በቤተሰብ ላይ እንዳይመጣ ይፈልጋሉ፣ ይጥራሉም::

በጋሞ ጐፋ ከቤተሰብ ውጪ የመጣች ሴት በገባችበት ቤት ውስጥ ሕፃኗን ብታጠባ በቤት ውስጥ ባሉት ልጆች ላይ አስማት በማድረግ እንደምትወስዳቸው ይታመን ነበር:: በተለይ የሚጠባው ልጅ ወንድ ከሆነ የበለጠ አደገኛ እንደሆነ መገመት የቤተሰብ ጥብቅ ሥርዓት ነበር:: የእናቱን ጡት መጥባቱ በቤት ውስጥ በነበሩት ሰዎች ላይ ልዩ ኃይል እንዲኖረው ያደርጋል ተብሎም ይታመን ነበር::

በቁጫም ተመሳሳይ ባህል ስለነበረን የሕዝቡን ጠቅላላ አሳብ የምናውቅና የምንጠነቀቅ ስለሆነ ወደ ጐፋ በገባን ጊዜ ስለሚገጥመን ባህላዊ ነገር ብዙም የምንፈራው አልነበረም::

## የመጀመሪያው ባሕልን ያለመረዳት ችግር

«ይህች ሴት ዘመድህ ነች? ብላ ከጐረቤት የገባች ሴትዮ ጠየቀችኝ::» በአስፈሪ ድምጿ ኀጉታ ስትጠይቀኝ ባሰቤቴን በጨረፍታ ገልመጥ አድርጌ ካየሁአት በኋላ ልጃችን እያጣጣመ የእናቱን ጡት ይጠባ ነበርና ስለ እርሱ ምንም የማስበው ነገር አልነበረም::

«ዘመዴ አይደለችም:: ከዛሬ በፊት አይቼአትም አላውቅም፣ ግን ለምን ጠየቅሽኝ?» አልኳት::

በእሳቱ ዙሪያ ተቀምጣ የነበረችዋ ሴት አዲስ ድምፅ ስትሰማ እንግዶች መሆናችንን ስላላስተዋለች ምናልባት እርሷ ያሰበችው ከጉጉት የተነሣ የቀረበ ጥያቄ አድርጋ ነበር:: በባህላዊ ወፍጮ ሥር ተንበርክካ የወፍጮውን መጅ ወደፊትና ወደኋላ በማንቀሳቀስ ለእራት የሚሆን በቆሎ መፍጨት ጀመረች::

«ዘመድህ ካልሆነች ታዲያ፣ እንዴት ልጇን በቤት ውስጥ ታጠባለች?» አለችኝ::

ሴትየዋ ጥያቄውን ገና ከአፏ እንዳወጣች ሌላዋ ሴት ቆመችና ሁለት እጆቿን በራሷ ላይ በማድረግ ወደ ውጪ በጥድፊያ ወጣችና «ኡ ኡ ኡ» ብላ መጮህ ጀመረች::

እኔ ደግሞ በባለ ሦስት እግር በርጩማ በእሳቱ ዳር ተቀምጬ ነበር:: ሴትየዋ ፈጥና ወደ ቤት በመግባት ወደ እኔ ተጠጋችና ከታች የተቀመጥኩበትን በርጩማ ሳብ ስታደርግብኝ ተገልብጬ በመሬት ተከመርኩ:: «እኔ ሞቻለሁ! እኔ ሞቻለሁ! ምንድን ነው ያደረጋችሁብኝ? ለምንድን ነው ጠላት የሆናችሁብኝ? ለምንስ ይህን ታደርጋላችሁ? ኡኡ! ኡኡ» ብላ እየጮኸች በተቻላት ፍጥነት ወደ ውጪ ልታወጣን ትጐትተን ጀመር::

ወደዚህ ቤት በገባን ጊዜ እኔና ባሰቤቴ ከሌሎቹ የቤተሰባችን አባሎች ተለይተናል:: አብረውን የነበሩት ሰዎች ከዝናቡ የተነሣ ወደ ዮሐንስ ቦታ እስኪደርሱ ድረስ ጉዞአቸውን ቀጥለዋል::

በዚያች ቅጽበት ሁኔታዎች ፈጥነው ተሰወጡና ሴትየዋን ዝም ለማሰኘት የምናደርገው ጠፋን::



በሚቀጥለው አጭር ጊዜ ውስጥ ጐረቤቶች ሁሉም በቤቱ ሲሰበሰቡ ሴትዬዋ ፀጥ ለማለት ባለመቻልዋ የተሰበሰቡት ሰዎች ወደ እኔ ዘወር ብለው ምን እንደ ሆነች ወይም ምን እንደ ተፈጸመ ጠየቁኝ:: እኛም በተቻለን መጠን ምን እንደ ተፈጸመ አስረዳናቸው::

የተሰበሰቡት ሰዎችም፣ «ልክ ነው:: ልክ ነው:: ልጆቿ ሁሉም በተለያየ መንገድ ሊሞቱ ይችላሉ» እያሉ አባባሱት::

ሴትየዋም የምትጮህበት ምክንያት እኛ ለቤቷና ለቤተሰቧ መጥፎ ዕድል ይዘን የመጣንባት ስለመሰላት ነውና እኛም የተከሠተውን ሁኔታ ስናስተውል ደንግጠናል:: የእኛ ወደ ጐፋ መምጣት ለሰዎች ሕይወትን ለማምጣት ሲሆን፣ ገና በመጀመሪያው ቀናችን በጐፋ ሥራችን እንደ ሰይጣን ሥራ ተተረጐመብን::

ምን ማድረግ እንደምንችል ግራ ስለተጋባሁ፣ ባለቤቴን፣ «አሁን ምን እናድርግ? ምናልባት በራሳችን መንገድ እንሂድና የአካባቢው ሰዎች ችግሩን ይለዩት ሌላ እኛ ማድረግ የምንችለው ነገር የለም» አልኳት::

ባለቤቴ ግን በጣም ፈራች:: የዚያ ሁሉ ችግር ምክንያት ራሷ እንደሆነች ቆጠረች:: እኔም ጌታ አምላካችን ይመለከተናል:: ይህ ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ሊሆን ይችላል ብዬ አረጋገጥኩላት::

እንዲሁም ደግሞ የቃላት አጣጣል ወይም የቋንቋ አነጋገር ስልትና የቃላት መጠነኛ ልዩነቶች ቢኖሩም ቋንቋችን በመሠረቱ ተመሳሳይ ነው:: እነርሱ የሚናገሩትን እንረዳለን፣ እነርሱም እኛ የምንናገረውን ይረዳሉ:: ለባለቤቴ ጉዞአችንን እንቀጥላለን ብዬ ስናገር ስለ ሰሙ ይህ የማይሞከርና የማይቻል ነው አሉ::

«ታዲያ ምን እንድናደርግ ትፈልጋላችሁ? እንዴትስ እንርዳችሁ? ጐፋ የመጣነው ሰላም ለማምጣት ነው እንጂ መከፋፈል፣ ሁከትና ጠብ ለማምጣት አይደለም:: ነገሩን እንዴት ማስተካከል እንደምንችል ንገሩን» አልናቸው:: «ይህንን አለመግባባት ሁሉ ለመፍታትና ለማስተካከል አድርጉ ያላችሁን ማንኛውንም ነገር እናደርጋለን» አልኳቸው::

«የአባቶቻችን መንፈስ ታወከና ተከፋ» ብለው ከተሰበሰቡት ሰዎች መካከል አንዱ ሰውዬ ተናገሩ:: ይህንን ቤት የሚያድነው የቤተሰብ መንፈስ በጣም ተቆጥቷል፤ ምክንያቱም እናንተ የሠራችሁት ነገር ነው:: ቢሆንም ሁኔታው ተስፋ የሌለው አይደለም:: «ስለዚህ ምን

እናድርግ? ይህ ሁሉ ነገር በተቻለ ፍጥነት እንዲያልቅ እፈልጋለሁ» አልኳቸው::

«ለተቆጣው ለሰይጣኑ መንፈስ የምንሠዋውን የመሥዋዕት በግ ስጡን» አሉን::

«ይህንንማ ማድረግ አልችልም» ሰይጣንን ክጄ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኜአለሁ:: ተቆጥቷል የምትሉትን የሰይጣንን መንፈስ አልፈራም ከቁጫ ወደ ጉፋ የመጣሁት መልካሙን ዜና ( ወንጌልን ) ለመስበክ ነው:: ይህም ዜና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍርሃት ነፃ እንዳወጣን የሚያበስር ነው:: አሁን እናንተ ሰይጣን እያላችሁ ለምትጠሩት የመሥዋዕት በግ እንዳቀርብ ጠይቃችሁኛል መሥዋዕት የማቀርብበትና ከመሥዋዕቱም የምካፈልበት አንዳች መንገድ አይኖርም::»

የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ከሰሜን ወደዚህ አካባቢ ከብዙ ምእተ ዓመት በፊት ሲመጣ ሰዎች ይህንን ክፉ መንፈስ ሰይጣን ብለው ጠሩት፣ የቃሉ ትርጉም ሲታይ ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ የተገኘ አልነበረም::[1]

«እኛ ግን ጠንቋይ ወይም ሞራ ገላጭ እንላለን፣ ይህን መሥዋዕት አቅርባችሁ የሰይጣኑ መንፈስ ቁጣው ከበረደ ያኔ መሄድ ትችላላችሁ፣ ቁጣው ካልበረደ እንደገና ሌላ በግ ታቀርባላችሁ» በማለት ቀጠሉ::

ለእንዲህ ዓይነት ሥርዓት እኔ እንግዳ አልነበርኩም:: የሰይጣኑ መንፈስ እስኪረካ ድረስ ብዙ በጐች እንደሚታረዱ አውቅ ነበር:: ነገር ግን ከሰይጣን ቁጣና ፍርሃት ለማምለጥ ተብሎ የጠየቁንን ለመስጠት ምንም አሳብ አልነበረንም:: ያንን መንፈስ ለማጥላላትና ለመከራከር አጋጣሚው ጥሩ ስላልሆነ በመጀመሪያ ከፍርሃታቸው እንዲረጋጉ ማድረግና ምንም ነገር እንደማይደርስባቸው ማረጋገጥ ይገባል:: ምክንያቱም በፍርሃት የሰይጣንን መንፈስ[2] ያስተናግዱ ስለነበር ነው::

ባለቤቴና ሕፃኑ ልጄ ከቤቱ ውጪ እንዲቀመጡ ካደረጉ በኋላ፣ እጆቼን ወደኋሊት ጠፍረው በማሠር ዳኛ ብለው ወደሚጠሩት ቤት ወሰዱኝ:: ዳኛውም በቤት አልነበሩምና ምን እንደሚያደርጉኝ ግራ ተጋቡ::

ነገሩን እርስ በርስ ከተወያዩ በኋላ ዳግመኛ ወደ እኔ መጥተው፣ «ባለቤትህ ሕፃኑን ያጠባችው በቤት ውስጥ ነው?» አሉና ጠየቁኝ::



ይህንን እኔ ብክድ ችግሩን እንደሚፈቱ ብረዳም አንድ ምስክር ብቻ ሊኖር ይችላል ያም እርሷን ለማሳመን ቀላል ሊሆን ይችላል:: ስለዚህ የተፈጸመውን ሁኔታ ለመካድ ግን አማራጭ ሆኖ የተከሰተልኝ አሳብ አልነበረም:: «አዎን፣ ልጃችንን በቤት ውስጥ አጥብታለች» ብዬ መለስኩኝ:: እነርሱ እንድክድ ዕድል ሰጥተውኝ ቢሆንም፣ እኔ ግን አልተቀበልኳቸውም:: እውነትን መናገር ነገርን ሁሉ የሚያባብስና ለእያንዳንዱም ሰው ችግር የሚፈጥር ይመስላል::

«ስለዚህ መሥዋዕት የምናቀርበውን በግ አሁን ስጠን» አሉ::

«ይህንን ካላደረግክ በዚህ ቤተሰብ ውስጥ ያሉት ልጆች በሙሉ በሰይጣኑ መንፈስ ሊገደሉ ይችላሉ» ብለው መወትወት ጀመሩ::

«እኔ ደሃ መንገደኛ መሆኔ ለእናንተ ግልጽ ነው:: በግ የለኝም:: በግ ለመግዛትም ገንዘብ የለኝም:: ስለዚህ ምን ላድርግ?» አልኳቸው::

ለመደራደር ጊዜው ደረሰ:: እውነታውም ግልጽ ስለሆነ ወንጀሉን ተናዘዝኩለሁ:: ሰዎቹም ይህንን አጣብቂኝ ለመፍታት አንድ መንገድ ብቻ ነበራቸው::

«የመሥዋዕቱን በግ አሁን ልትሰጠን ካልቻልክ፣ ዋስ መጥራት ይኖርብሃል:: ቀጠሮም ለጥተኽን በጉን ታመጣልናለህ» አሉና ተከራከሩኝ::

ይህ ለእነርሱ ቀላል ሊሆን ይችላል፣ ግን በእንግድነት አገር ዋስ የሚሆነኝን ሰው የት አገኛለሁ?

ተቀምጬም ማሰብ ጀመርኩኝ:: «ሄጄ ሰው እንድጠራም አይለቁኝም:: እርዳታ እንደምፈልግ ካልተረዱ ወደ እኔ የሚመጣም ስለሌለ እንዴት ዋስ ማግኘት ይቻለኛል?»

## በዋስ መፈታት

በዚያን ወቅት የሐጬሶ አባት ተብለው የሚታወቁ ነጋዴ ከቁጫ ሲመጡ በማየቴ በጣም ደስ አለኝ:: ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ስለየቤተሰቦቻችን ከተጠያየቅን በኋላ ሁላችንም ለጤናችን ደህና ነን፣ ግን ብዬ ሁኔታዎቹን በዝርዝር ገለጽኩላቸው::

«የዚህን አካባቢ ሰዎች አውቃለሁ:: እነርሱም ያውቁኛልና እኔ ዋስ እሆንሃለሁ፣ ችግር የለም ብለው አደፋፈሩኝ::

የመንደሩን ሽማግሌዎች ጠርቼ የሐጤሶ አባት ዋስ ሊሆኑኝ እንደሚችሉ ስነግራቸው በአሳቡ ተስማምተው በአንድ ሳምንት ውስጥ በጉን እንዳቀርብ ነገሩኝ። እኔ ቀጠሮዬን አክብሬ በተባለው ሳምንት ባላቀርብ ዋስ የሆኑኝ የሐጤሶ አባት በጉን እንደሚሰጡ ተናገሩ።

«ምን ባደርግ ይሻለኛል? ምንስ ማድረግ እችላለሁ?» ችግሩ ገና ባይቃሰልም መፍትሔ ለመሻት ግን የአንድ ሳምንት ጊዜ አለኝ። ወንድሜ ዳንኤልና እኅቴ መስቀሌ ወደ አቶ ዮሐንስ ቤትና ወደ አቶ ዳሮታና አቶ ዓለሙ ከልሌ ዘንድ ሲደርሱ በመጨረሻም እኛም ሩቅ ቦታ እንዳልሆንን አውቀዋል። ከሌሎች መንገደኞችም ዘንጋ ወደሚባል መንደር እንደደረስንም ሰምተዋል።

እንደ አካባቢያችን ባሕል አንድ ሰው ተሰይቶ በሚሄድበት ጊዜ ሁላችንም እጅ ለእጅ ተጨባብጠን መልካም ጉዞ እንዲሆንለት እንመኝና እንሰናበተዋለን። እናም በዛንጋ የነበሩት ሰዎችም በተመሳሳይ ሁኔታ ተሰናብተው ሸኙን። ጥቂት ተጉዘን ወደ ካሪዛ ወደሚገኙ ወዳጆቻችን ቤት ደረስን።

የደረሰብንን ችግር ስንነግራቸው አቶ ዓለሙ በጣም ተቆጡ። «እነማን ነበሩ? ያሠሩአችሁ ሰዎች ስማቸው ማን ማን ይባላል? ወደ አገራችን በመጡት እንግዶች ላይ እንደዚህ ዓይነት ነገር መፈጸም ምን ይባላል? ቆዩ የማደርጋቸውን እኔ አውቃለሁ» አሉ።

ባላባትና የመሬት ከበርቴ እንደ መሆናቸው በአካባቢው ሰዎችን በማንገላታት የፈለጉትን እንዲያደርጉ ማዘዝ የሚችሉ ነበሩ። የእርሳቸው እርምጃ ችግራችንን የሚያቃልል ሳይሆን የሚያባብስ መስሎ ተሰማኝ።

«እባክዎ፣ ምንም አይበሉ» ብዬ ለመንኳቸው። «ለጊዜው ግን ነገሩ አብቅቷል። በማንኛውም መንገድ ሰዎቹ ይጎዱናል ማለት አይደለም። ነገር ግን ባለማወቃችን ባሕላቸውን ተዳፍረናል። ስለዚህ እባክዎ ምንም አይናገሯቸው። በመካከላችን የከረረ ችግር እንዳይከሠት ሁኔታውን ለማቃሰል ሌላ መንገድ እንፈልጋለን» አልኳቸው።

አቶ ዓሰሙ ወደ ዛንጋ ላለመሄድ ተስማሙ። እኔም በጉዳዩ ምን ማድረግ እንደምችል ለመጸለይ የአንድ ሳምንት ጊዜ ነበረኝ።



በቀጠሮዬ መሠረት በስምንተኛው ቀን ተነሥቼ ወደ እነዚያ ሰዎች ስሄድ የሐጤሶ አባትም እዚያ ነበሩ። የመጀመሪያው ኃላፊነቴ እርሳቸውን ማስፈታት ነበር።

ለተሰበሰቡት ሰዎችም፣ «ቀጠሮአችንን ለዛሬ አድርገን ነበር አልኳቸው። ይኸውና መጥቻለሁ፣ ዋስ የሆኑኝ ሰውም ይኸውና አሉ። ምላሽ ለመስጠት ነው የመጣሁት። ዋስ የሆነኝ ሰው በነበረው ውዝግብ ውስጥ አልነበረም። በወቅቱ እርሱ አብሮን አልነበረም። የነበርኩት እኔ ስለሆንኩ በኃላፊነት መጠየቅ የሚገባኝ እኔ ነኝ ትስማማላችሁ?» አልኳቸው።

መስማማታቸውን ለመግለጽ ራሳቸውን ከፍ ዝቅ አደረጉ።

«እንግዲያውስ ዋስ የሆነኝ ሰው አሁን ይለቀቅ፣ በማንኛውም ጉዳይ ላይ በኃላፊነት የሚጠየቅበት ነገር የለም፤ ትስማማላችሁ?» አልኳቸው። አሁንም በሃሳቤ መስማማታቸውን ራሳቸውን ከፍና ዝቅ በማድረግ ገለጹ። አሁን መልስ ልሰጣቸው ነፃ ነኝ።

በነበረው አጋጣሚ የተፈጠረው ክስተት ከባሕላችን የተነሣ ነው። ወደዚህ አለመግባባት ስላመጣን ነገር ከሥሩ ጀምሬ ማስረዳት ጀመርኩኝ። ጊዜ እንደሚወስድ ባውቅም በተሰበሰቡት ሰዎች መካከል ግን ውጤቱ ጥሩ ግንኙነት ሊገነባ እንደሚችል አሰባለሁ። አድማጮቼ ሁሉም በታሪኩ ተሳታፊ መሆን ጀመሩ። አለመግባባትን ባመጣብን መጥፎ ሁኔታ ላይ ብቻ አልነበረም፣ እርግጥ ነው ለዛሬ ቀጠሮ ይዘናል፣ ቃሌንም ጠብቄ መጥቻለሁ፣ ለክሴም መልስ ለመስጠት ተመልሻለሁ።

«አገሬን ወይም ይህንን ሕብረተሰብ የሚጎዳ ወንጀል አልፈጸምኩም። ከፈለጋችሁም መስቀለኛ ጥያቄ ልታቀርቡልኝ ትችላላችሁ። ልታሥሩኝም ከፈለጋችሁ፣ እሠሩኝ። መጣላትና እሥራትን መቃወም አልችልም። የፈለጋችሁትን ልታደርጉ ትችላላችሁ። ይኸው ተመልሼ ወደ እናንተው መጥቻለሁ። አሁን በእጃችሁ ውስጥ ነኝ።»

ማንም ቃል አልተናገረም። ፊታቸው በአጠቃላይ የረጋ ነበር። በቁጣ የተጨማደደ ፊት አልነበራቸውም።

የተቃወመችን ሴትዮ ባሰቤት ተቆጥቶ እንደነበር ለእኔ ግልጽ ነበር። ዮሐንስ አብሮኝ ነበር። በምንም ዓይነት መንገድ መሥዋዕት

ሳስመቅረብ ተስማምተናል። ሰተወሰነ ጊዜ ሰዎቹ አልተስማሙም። እኛም መሄዳችን ነው ስንላቸው ሊያግዱን አልሞከሩም።

ዮሐንስም፣ «እንሂድ» አለኝ።

ለሰዎቹም እንግዲህ መልሳችንን ሰጥተናችኋል፤ ሌላ የምንለው ነገር የለንም ብለን ለመሄድ ምንም ፍቃድ አልጠየቅናቸውም። የራሳችንን ውሳኔ ወሰንንና የሚከተለንን ሁሉ ለመቀበል ተነሣን። አሁንም እንዳንሄድ ሊያግዱን ያደረጉት ጥረት አልነበረም። ዳሩ ግን ፍላጐታቸው ባለመሟላቱ ምንም አላረካቸውም ነበርና በምሬት ቅሬታቸውን ማሰማታቸው ግን አልቀረም። እኔና ዮሐንስ በሰላም ወደ ካሬዛ ተመለስን።

በመጨረሻ እንደሰማነው የተቃወመችን ሴትዮ ባል ስለ መሥዋዕት ጉዳይ ግፊት አድርጎ ነበር። በባለቤቱ ድርጊት ተቆጥቶ የነበረውን የሰይጣንን መንፈስ ለማስደሰት ቢፈልግም በጥቂት ጊዜ ውስጥ ሰውየው ሞተ።

ከጥቂት ወራት በኋላ ሴትዮዋ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አመነች። ልጇም ጉሳዬ የሚባል ወንጌላዊ አገባች። ሴትዬዋ እስከ ዛሬ በሕይወት ትኖራለች፣ በአካባቢዋም ባለው ቤተ ክርስቲያን ጌታን እያገለገለች ትገኛለች። በአሁኑ ጊዜ በዛንጋ አካባቢ ብዙ የጸሎት ቤቶች ተመሥርተው ይገኛሉ።

# አቶ መሐሪ በጐፋ የወንጌል ሥራን ጀመሩ

በጥቅምት ወር 1941 ዓ.ም ለአጭር ጊዜያት በካሬዛ ቆየን። ዮሐንስ እዚያ ቤት ነበረውና አቶ ዓለሙ (ባላባትና የመሬት ከበርቴ የነበሩት) ለሁለታችንም ለእርሻ የሚሆን መሬት ሰጡን። በሕዳር ወር 1941 ዓ.ም በጐፋ በአቶ ዓለሙ መሬት ላይ የመጀመሪያውን ጸሎት ቤት ሠራን። ቤቱም የሠላሳ ሜትር ስፋት ነበረው።

በካሬዛ ለተወሰኑ ወራት ከሠራን በኋላ፣ ባጐ ወደሚባለው ወደ ሌላ ስፍራ ለመዛወር በራሴ ወሰንኩ። ይህ ቦታ ከቡልቂ ከተማ አንድ ሰዓት ከሩብ ያህል በእግር ያስኬዳል። በእርሻችን ላይ እህል ያመረትን ስለሆነ እስክንሰበሰብ ድረስ ባለቤቴ በካሬዛ እንድትቆይ ወሰንን።

የእያንዳንዱን ቦታ ስም በዝርዝር ባልጠቅስም፣ በዚህ አካባቢ ስዘዋወር እግዚአብሔር ያስቀመጠኝ ሰባተኛ ቦታዬ ነበር። በቁጫ



ውስጥ በጐበ፣ በቦሎሻ፣ በጋላ እና በሞርካ፣ እንዲሁም ለጥቂት ጊዜ በጐፋ ውስጥ በሜላ በካሬዛና አሁን ደግሞ በባጋ እየሠራሁ ነበር።

በባጋ ችግርና መልካም ነገር ነበር። እርሻዬንና ከብቶቼን በቁጫ ትቼ ወንጌልን ለመስበክ ወደ ጐፋ ሄድኩኝ። ከዚያም በድንገት ታመምኩ። ሦስት ዓመት ሙሉ በጠና ስታመም የምድንም አልመሰለኝም ነበር። እኔ በሕመም በነበርኩበት ጊዜያት ጌታ ይሠራ ስለነበረ በጐፋ ብዙ ተጨማሪ ጸሎት ቤቶች ተመሥርተዋል።

ለመጀመሪያ በ1941 ዓ.ም ወደ ጐፋ በሄድን ጊዜ በ1922 ዓ.ም በሚስተር ኦህማን ጊዜ ተጠምቀው የነበሩትን አንድ ወይም ሁለት ሰዎች ማፈላለግ ጀመርኩኝ። በኋላም ጐፋ ኃይሌ እና የሱስ ኃይሌ፣ እንዲሁም ደፋርሻ የሚባሉትን ሰዎች አገኘሁ። እንዲሁም ከአሪ ጐሳ ጐጋ የሚባለውን አማኝ ነኝ ብሎ የሚያወራውን ሰው አገኘሁ። እነዚህ ሰዎች ሁሉም በ1928 ዓ.ም የውጪ አገር ሚስዮናውያን ጐፋን ለቅቀው ከሄዱ ወዲህ ምንም መንፈሳዊ ስብሰባ አዘጋጅተውና ተሰብስበው አያውቁም ነበር። በወላይታ ከሚገኙት ወንጌላውያን ጋር ራሳቸውን ለማስተዋወቅ ያደረጉት አንዳች ጥረት አልነበረም። በ1941 ዓ.ም ወደ ጐፋ በሄድን ጊዜ እነዚያ ሰዎች ከመንፈሳዊነት ወደ ዓለማዊነት ተለውጠው እንደ ዓለማውያን ይኖሩ ነበር። ጠንቋዮች የሚያዟቸውን መሥዋዕት ሁሉ ያቀርቡላቸው ነበር። በጌታ ጸጋ ብቻ ንስሐ ገብተው ዳግም ወደ እርሱ ተመልሰዋል።

*ማስታወሻ*

1. የሐሳብ ሽግግሩን ለመከተል አይቸግርም፦ እነዚያ የቤተሰብ መናፍስት የእግዚአብሔርን ታማኝነት ይቃወማሉ። እግዚአብሔርን ስለሚፈታተኑት የሰይጣን አገልጋዮች ናቸው።
2. ዘፍጥረት ምዕራፍ 18።

*በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አቶ መሐሪና ጓደኞቻቸው በሰሌዳ ላይ የሳሉት የቤተ ክርስቲያን ተክላ ንድፍ ባይኖራቸውም፣ የራሳቸው የአገልግሎት ዘዴ ግን ነበራቸው። በቀላሉ ኢየሱስ ከነተከታዮቹ ያደረገው ነው ብለው የሚያምኑትን ሁሉ ያደርጋሉ። ብራዬን ፋርገር*

# ቤተ ክርስቲያንን የመትከል ዘዴ

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት

የወላይታ ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያንን ለመትከል ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን ይጠቀማሉ፣ ወንጌል ሥርጭትና በዓል ማድረግ። የመጀመሪያ ነጥባቸው ሰዎች አብሮአቸው ካደገው የኃጢአት ፍርሃት እንዴት ነፃ እንደሚወጡ በግልጽ ማስረዳት ነው። በመካከላቸው እየተዘዋወሩ የሚያስተምሯቸው ሰዎች እግዚአብሔር ፈጣሪ እንዳለ እንዲያውቁና አንድ ነገር ከእግዚአብሔር እንደለያቸውም እንዲረዱ ማድረግ ነው። የወንጌላውያኑም መልእክት መልካም ዜናን የሚያበስርላቸው ሲሆን፣ መልካም ዜና ማለትም ወንጌልን ማብሰር የወንጌላውያን ቀዳሚ ሥራቸው ነው።

ሰዎች መልእክታቸውን ከተቀበሉ በኋላ በኅብረት እየተሰበሰቡ እንዲያመልኩ ይነግሯቸዋል። የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በጸሎት ቤት ይካሄዳል። በየቤታቸውም የእግዚአብሔርን ታላቅነት በየማኅበራቸውም ሁሉ አገልግሎቱ በስፋት ይከናወናል።

የመጀመሪያዎቹ የኤስ ኣይ ኤም የውጪ አገር ሚስዮናውያን ራሳቸውን መልእክተኞች እንጂ የቤተ ክርስቲያን ማዕከል አድርገው አልገመቱም፣ ለአዲስ ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ ፍሬ ሆነው ለመታየት ያደረጉት ጥረትም አልነበረም። ወንጌልን አስተምረው ሰዎችን ካጠመቁ በኋላ ከዚያ አካባቢ ይወጣሉ። ይህንንም የሚያደርጉት የአዳዲሶቹ አማኞች ኅብረትም ቤተ ክርስቲያን ይሆናሉ ብለው ስለሚያስቡ ነበር። ኢትዮጵያውያን ወንጌላውያን ግን እንደዚህ አያደርጉም። በሚሠሩበት በየትኛውም ቦታ የአዲስ ቤተ ክርስቲያን ማዕከል ያቋቁማሉ።

የወንጌላውያኑ ረዥሙ የሥራ ዕቅዳቸው በሚቻላቸው መንገድ ለብዙ ሕዝብ ወንጌልን መስበክ ነው። በቁጥር አነስተኞች እንደሆኑ ስለሚያውቁ የአካባቢው ሕዝብም በስብከት እንዲሳተፍላቸው ይሻሉ።



በአንድ አካባቢ የመጀመሪያው ክርስቲያን በብዙ ጥረት ከተማረና ከተጠመቀ በኋላ በዚያው ቦታ የሥራው መሪ ይሆናል። የመጀመሪያው ጸሎት ቤትም በራሱ መሬት ላይ ይሠራል። ሰውየውም ብዙውን ጊዜ የማኅበሩ አስተማሪና ሽማግሌ ሆኖ ያገለግላል። ይህ ዘዴ ከድክመት ይልቅ ብርታትን ስላመጣ ለአያሌ ዓመታት ሲቀጥል ችሏል።

ጥቂት ሰዎች ካመኑ በኋላ ጸሎት ቤታቸውን ለየት አድርገው ይሠራሉ። ብዙውን ጊዜ ዙሪያውን አጥረው አበባ በመትከል ያሳምሩታል። ቤቱ የሚያገለግለው ለአምልኮት ብቻ ሲሆን፣ ቤቱ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ጋር በፍጹም አይመሳሰልም።

የመጀመሪያዎቹ ወንጌላውያን አዳዲስ አማኞችን ያጠምቁ ነበር። ነገር ግን አንዳንድ ቦታ ሰዎች ሽማግሌ ሆነው እንደተመረጡ የማጥመቁን ተግባር ራሳቸው ማከናወን ጀመሩ። ጠፍጣፋ ቂጣና ማር በውኃ ተበጥብጦ በወር አንድ ጊዜ የቅዱስ ቁርባን ሥርዓት ይከናወናል። ቅዱስ ቁርባን እንዲወስዱ የሚፈቀድላቸው አምነው የተጠመቁት ብቻ ሲሆኑ፣ አንዳንዶቹ የራሳቸውን ሥርዓት በማከል በርና መስኮታቸውን በመዝጋት በምሥጢር ኅብስቱን ይቆርሳሉ፣ ከጽዋውም ይጠጣሉ።

ሥነ ሥርዓቱ አብዛኛውን ጊዜ ዝማሬንና ስብከትን ጨምሮ ሦስት ሰዓት ያህል ይወስዳል። ዝማሬ በድምፅ ብቻ ሲሆን፣ በነአቶ መሐሪ ዘመን ከበሮና ሌሎችም የሙዚቃ መሣሪያዎች ለባሕላዊ ጭፈራዎች የሚጠቀሙበት ስለነበረ በቤተ ክርስቲያን አይፈቀድም ነበር። መዝሙሩን ወንዶችም ሴቶችም በየተራ ሲመሩ፣ ብዙውን ጊዜ ሰዎች በእርሻ ቦታቸው ሆነው በኅብረት ከሚያዜሙት ጋር ይመሳሰላል። ማንበብ የሚችሉና በጣምም ያልተማሩ ሰዎች በዚያን ጊዜ ይሰብካሉ፣ ሆኖም ግን ሴቶች አይሰብኩም ነበር። የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በዚያን ወቅት በአምልኮ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት አክለው ስለማይሰብኩ አዳዲሶቹ ቤተ ክርስቲያኖች ለስብከታቸው የሚስዮናውያንን መልእክቶች ምሳሌነት ይከተላሉ። መልእክታቸውም አብዛኛውን ጊዜ ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተውጣጡ ሲሆኑ፣ ተመሳሳይ አሳብ ያዘሉ ይሆናሉ። ምክር አዘል ንግግሮች ጊዜ በመውሰድ እንዲተላለፉ የሚደረግ ሲሆን ይተላለፋሉ።

አንዳንድ ወንጌላውያን ለአጭር ጊዜ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች በመሆን ያገለግላሉ:: እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ይህንን ሁሉም ወንጌላውያን የማይቀበሉት ነው:: የእነርሱ ጥያቄና ተልዕኮ እየተዘዋወሩ ወንጌልን ማገልገል ነው::

በአካባቢው የጸሎት ቤቶች እየተጨመሩ ሲሄዱ ወንጌላውያን ከወላይታ ቤተ ክርስቲያን የወረሱትን ድርጅታዊ አሠራር ይከተሉ ጀመር:: ስለዚህ የጸሎት ቤቶችንም በሦስት ክፍሎች በመክፈል አደራጅተዋል:: ስድስት የተመረጡ ሰዎች በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባሉ፤ እንዲሁም የሠላሳ ሰዎች ቡድን በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባሉ:: ሦስተኛው ቡድን የወረዳ ቦርድ ሲሆን ከሁሉም ቤተ ክርስቲያኖች ተወካዮች በአካባቢው በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባሉ::

በ1930ዎቹ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ለገንዘብ ሲሉ መሥራት አልተለመደም ነበር:: ቤቶቻቸውን ለቅቀው ወደ ሌላ ቦታ ሄደው የሚሰብኩ ወንጌላውያን መሬት ተከራይተው የራሳቸውን እርሻ በማረስ ምግብ ያገኙ ነበር:: ይህን ካላደረጉም ይራባሉ:: ከወላይታ ማኅበራት የሚላኩት ግን መደበኛ ያልሆነ አነስተኛ ገንዘብ ለልብሳቸውና ለመጓጓዣቸው ወጪ ይቀበላሉ::



## *ወደ ምዕራፍ አሥራ ሦስት መግቢያ*

*በምዕራፍ አሥራ ሦስት ውስጥ አቶ መሐሪ አገልግሎታቸው የችግር አሻራ ትቶ ያለፈ እንደሆነ አሳባቸውን ያስተላልፋሉ:: መቼም ከእውነት የሚርቅ ምንም ነገር የለም:: በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አንባቢያንን ከትክክለኛ ሕይወት ጋር ለማያያዝ ይሞክራሉ:: ማማረራቸውና ቅሬታቸውን መግለጻቸው አይደለም ወይም የኀዘን ስሜታቸው እንዲገለጥ ለማድረግ አይደለም:: የእርሳቸው መነሣሣት ችግርን ለመቀስቀስ መስሏቸው አንባቢያን ሊረበሹ ይችላሉ:: አሁንም ከእውነት ሊርቅ የሚችል ምንም ነገር የለም:: በቃሉ ስሜት እርሳቸው ሰላም አምጪ ነበሩ::*

*አቶ መሐሪ በአስደናቂ ሁኔታ ብዙ ጊዜ ሕመምና እሥራትን ተለማምደው አልፈዋል:: በእርግጥ ብዙ ወንጌላውያንም ተመሳሳይ ሁኔታ ገጥሟቸዋል:: በእነዚህ ፈተናዎች በተለይም አቶ መሐሪ ሁለት ነገሮችን ተለማምደዋል ይኸውም፦ አገልግሎትና ተአምራት ናቸው:: በእስራትና በሥጋዊ ድክመትም ውስጥ እንኳ ሆነው አገልግሎታቸውን በብቃትና በኃይል ያከናውኑ ነበር::*

*በደቡባዊ ኢትዮጵያ ሕዝብ የቀን አቆጣጠር ሥርዓቶች የቀብር ሥነ ሥርዓቶች በጣም አስፈላጊ ክስተቶች ናቸው:: ክርስቲያኖች በጣም ለየት ያለ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችሉት በቀብር አጋጣሚ ነበር:: በኅብረተሰቡ መካከል የማኅበራዊ ግንኙነት ፀሮች ተብለው ይታወቃሉ:: ምክንያቱም በባሕላዊ የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ስለማይሳተፉ ነው:: የማይሳተፉበትም ዋናው ምክንያት ጉዳዩ ባህል ከመሆኑም ባሻገር መንፈሳዊ ሕይወታቸውን በእጅጉ የሚነካ ስለሆነ ነው:: በወቅቱ የእነርሱ አቀራረብ ውጤት አልባ የሆነ ይመስላቸው ነበር:: ግን እንደ እርሱ አልነበረም:: ነገር ግን ሞትን ለመረዳት የሚያስችል ኃይለኛ አዋጅ እንጂ::*

*በቡድኑ ውስጥ የውጪ አገር ሚስዮናውያንና ወንጌላውያን የማይናቅ ድርሻ አበርክተዋል:: የአገልግሎት በር ከፍተዋል፣ የአገር ውስጥ ወንጌላውያንን አበረታተዋል፣ ሥልጠናም ሰጥተዋቸዋል፣ ላቋቋሟቸው ማኅበራትም መሪዎችን አሠልጥነውላቸዋል::*

# መዝራትና ማጨድ

## ምዕራፍ አሥራ ሦስት

ስለ ራሴ ከመናገሬ በፊት ከ1942 - 1946 ዓ.ም ጌታ ወንጌላውያንን አነሣሥቶ በጎፋ ውስጥ በአራት አቅጣጫዎች ወንጌልን እንዲያሰራጩ አድርጓል። የተለያዩ ወንጌላውያን የሠሩባቸው ቦታዎች፡- ኡባ፣ ጎፋ፣ ዛላ፣ ወይያ፣ ያሎ፣ ማሎ፣ ማሾራ፣ ባስኬቶና ውብሐመር ይባላሉ፡፡ በእነዚህ ቦታዎች ወንጌል በይበልጥ የተሰራጨው እኔ ታምሜ በነበርኩበት ወቅት ነበር።

ከመታመሜ በፊት በዮሐንስ ቤት አጠገብ ትንሽ ቤት ሠርቼ ነበር፡፡ ታናሽ ወንድሜ ዳንኤል በራሱ ጥረት መጽሐፍ ቅዱስን በጥቂቱ ለማንበብ ከመቻሉ ውጪ በቂ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ባይኖረውም፣ ቃንጪ በሚባለው ቦታ ማኅበር ሽማግሌ እንዲሆን ተጠየቀ። ወደ ቀለም ት/ቤት ወይም ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በፍጹም ገብቶ አያውቅም። ዮሐንስ ደግሞ በካሬዛ ማኅበር ሽማግሌና ወንጌላዊ ሆኖ ነበር። በወቅቱ እኔ ባጋ ወደሚባለው ደጋማ አካባቢ እንድዛወር ወስነን ነበር፡፡

በጎፋ ስድስት ወር እየሰበክን ከቆየን በኋላ፣ የወላይታ ማኅበር ሽማግሌዎች ቦርድ ደመወዛችንን ዘጠኝ ብር ላኩልን፡፡ ያንን በመቀበላችን በጣም ደስ አለን፡፡

«ዘጠኝ ብር ለምን ያህል ጊዜ ይበቃል?» ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ጥያቄ እኛ አንጠይቅም፣ ምክንያቱም ይከፈለናል ብለን ስለማንጠብቅና የምንመገበውን የምናገኘውም ከእርሻችን ስለነበረ ነው፡፡ በቀን ሃያ አምስት ሳንቲም ሂሳብ ለአንድ ሠራተኛ ይከፈል ስለነበር ምናልባት የተላከልን ገንዘብ የስድስት ሳምንት ሂሳብ ሊሆን ይችላል። ማንም ሰው ስለሚከፈለኝ እሰብካለሁ ብሎ የሚያስብ አልነበረም።

እኔም በወባ ታምሜ የነበርኩት ያን ጊዜ ነበር፡፡ አንድ ቀን በማዛ ጫካ ውስጥ በምሄድበት ጊዜ ከባድ ዝናብ ዘነበብኝና ልብሴ ሁሉ በዝናቡ ራሰ፡፡ ሰውነቴም በጣም ብርድ ይሰማኝ ጀመረ፡፡ ያን ጊዜ ይመስለኛል በወባ ተይዤ በጠና የታመምኩት፡፡ በወቅቱ የስድስት ሜትር ስፋት ያለውን ቤት ለመሥራት ዕቅድ አድርጌ ቢሆንም፡፡ ታምሜ በጣም



ደክሜ ስለ ነበረ ሃሳቤን ለወጥኩና የሦስት ሜትር ስፋት ያለውን ቤት ለመሥራት ቻልኩ፡፡

በአገራችን ሰዎች ብዙውን ጊዜ ቤትን በኅብረት ይሠራሉ፡፡ ይህም ማለት ቤት ለሚያሠራው ሰው ሄደህ ታግዘዋለህ፡፡ አንተም ቤት ለመሥራት በምትፈልግበት ጊዜ በተራው መጥቶ ያግዝሃል ማለት ነው። ይሁንና እኔ ወደ ባጋ በተዛወርኩ ጊዜ ሁለት ችግሮች ነበሩብኝ። ማንም ሰው ቤቱን ሲሠራ እኔ ስላላገዝኩ፣ አሁን በተራዬ ቤቴን ስሠራ ማንም አላገዘኝም ነበር። ሁለተኛ፣ ለምሳሌ ሃያ ሰዎች ብታገኝ ጉድጓድ ለማስቆፈር፣ ግድግዳ ለማቆም፣ ከላይ ጣራውን ለማስተካከል ለሚረዱህ ለሁሉም በቂ ምግብና መጠጥም ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ እኔ ደግሞ ለዚያ ብዙ ሰው ምግብና መጠጥ ለማዘጋጀት ገንዘብ አልነበረኝምና ሌላ ምርጫ ስላልነበረኝ የራሴን ቤት ራሴ መሥራት ነበረብኝ፡፡

ይሁን እንጂ በገጠሩ የነበሩት ሰዎች ለእኔ ደግ ነበሩ። ለጣራና ለግድግዳ የሚሆን እንጨት ስለምናቸው ከዛፎቻቸው መካከል የፈለግኩትን እንድቆርጥ ፈቀዱልኝ፡፡ ለእንጨቱም ሆነ ለቤት መክደኛ ሣር ምንም አላስከፈሉኝም፡፡ ነገር ግን ለአያሌ ቀናት በጠና ታምሜ ስለነበረ መቆምና መራመድ ተሳነኝ፡፡ ስለዚህ እንጨት በምቆርጥበትና በማስተካክልበት ጊዜ ተቀምጬ እሠራ ነበር።

ለወባ የሚሆን መድኃኒት አልነበረም። ከአካባቢ ሰዎች መካከል የባሕል መድኃኒት ያውቃል የሚባለው ወባን ሊፈውስ የሚችል ነው ብሎ መራራ ጣዕም ያለውን ነገር በጥብጦ ሰጠኝ፡፡ ነገር ግን የተባለው መድኃኒት ምንም አልረዳኝም፡፡ ችግሩ ምን መሰላችሁ? በሽታዬ ወባ አልነበረም፡፡ ለካስ የሳምባ በሽታ ኖሯል፡፡ ሌላ መድኃኒት መሞከር አለብኝ ብዬ ወሰንኩ።

ፈለገ ንዋይ ወይም ሳውላ በሚባል አነስተኛ ከተማ ትንሽ ገበያ ይቆም ነበር፡፡ ወደዚያ ቦታ ሄጄ መድኃኒት ይገኝ እንደሆን ለመጠየቅ ፈለግኩኝ፡፡ ያን ጊዜ ደግሞ በቡልቂ ማንም ሚስዮናዊ አልነበረም፡፡ ለሁለት ቀን በጠና ታምሜ በዛፍ ሥር ተጋደምኩኝ። ያን ጊዜ ዶክተር ናታን ባርሎውና ሚስተር ዋልተር አህማን ለኤስ አይ ኤም ጣቢያ የቤትና የትምህርት ቤት የክሊኒክ ሥራን በጋሞ ጎፋ ለመጀመር የሚችሉበትን ቦታ ለማየት መጡ። እነርሱም ለአጭር ጊዜ የረዳኝን መድኃኒት ሰጡኝ።

በዚያን ጊዜ ባጋ በሚባለው አካባቢ ብዙ ሰዎች መጻፍና ማንበብ ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት የነበራቸው ቢሆንም፣ እኔ ከሕመሜ የተነሣ በጣም ይደክመኝ ስለ ነበር ላስተምራቸው አልቻልኩም። ከወላይታ የመጡ ሌሎች ሁለት ወንጌላውያን በአካባቢው ይሠሩ የነበሩ ቢሆንም፣ ሁለቱም አረ ሼፍታ ወደሚባል አዲስ አካባቢ በመዛወራቸው እኔ ብቻዬን ነበርኩኝ። በጣም ከመታመሜ የተነሣ ለመንቀሳቀስ እንኳን ችግር ነበረብኝ። ሁልጊዜ፣ «ምን ባደርግ ይሻለኛል?» እያልኩኝ ራሴን እጠይቅ ነበር።

## ለሕክምና ወደ ሶዶ

በመጨረሻም በወላይታ ወደሚገኘው ኤስ ኣይ ኤም ሆስፒታል ሄጄ ዶክተር ባርሎውን ለመገናኘት ወሰንኩ። ጉዞው በጠቅላላው የሚፈጀው አምስት ቀን ቢሆንም፣ እኔ ከድካሜ የተነሣ ቁጫ ደርሼ ካረፍኩ በኋላ ሶዶ ለመድረስ ሰባት ቀን ወሰደብኝ። ዶክተር ባርሎው ከመረመሩኝ በኋላ በትክክል ወባ እንዳለብኝ አረጋገጡልኝ። አስፈላጊውን መድኃኒት ከሰጡኝ በኋላ፣ ወደ ጎፋ ብመለስ ችግር እንደሌለ ነገሩኝ።

ይሁን እንጂ ጓደኞቼ፣ «በጣም ስለታመምክ በዚሁ ሁኔታ ወደ ጎፋ ብትመለስ ልትሞት ትችላለህ። ዶክተሩ ኦፕሬሽን እንዲያደርጉህ ማነጋገር አለብህ። ወደ ጎፋ መመለስ አይገባህም። ያን ያህል ርቀት ልትሄድ አትችልም፣ ታመሃል» አሉኝ።

እኔም፣ «እግዚአብሔር የሚገድለኝ ከሆነ እሞታለሁ ወደ እርሱም እሄዳለሁ። ስለኔ ማዘን አይገባችሁም። ሕይወቴ በእርሱ እጅ ነው ያለው። እግዚአብሔር እንድኖር ከፈለገኝ፣ እኖራለሁ። እንድሞትም ከፈለገ፣ እሞታለሁ። መኖርም ሆነ መሞት ለእኔ ይስማማኛል» ብዬ ነገርኳቸው። እንዳይጨነቁም አጽናናሁአቸውና በተቻለኝ ፍጥነት ወደ ጎፋ ለመመለስ ወሰንኩኝ።

ለመንገዝ በተዘጋጀሁም ጊዜ፣ አብሮኝ ሊሄድ የሚችል ማንም እንደሌለ አስተዋልኩ። ሁሉም ሰው ደግሞ ብቻህን መጓዝ በጣም አደገኛ ነው ይለኝ ነበር። ሰዎች በመንገድ እየተገደሉ ልብሶቻቸውን ይዘረፉ ነበር፣ ዘራፊዎቹም የዘረፉትን ልብስ ወደ አካባቢው ገበያ ወስደው በመሸጥ በገንዘቡ መጠጥ ገዝተው ይጠጡበት ነበር።

አንድ ሰው አብሮኝ ለመሄድ ፍቃደኛ ሆኖ የነበረ ቢሆንም፣ አድርሶኝ ለመመለስ ከፍተኛ ገንዘብ እንድከፍለው ከመጠየቁም በላይ፣



አመለካከቱም ጥሩ ስላልመሰለኝ አስብበታለሁ ብዬ መለስኩለት። እርሱን ትቼው ስለ ጉዞዬ ምንም ሳላስታውቅ በፍጥነት ከዚያ ተነሣሁና ጉዞዬን ቀጠልኩ። ብቻዬን ለመጓዝ እንደ ወሰንኩ እንዲያውቁብኝ አልፈለግኩም ነበር። በፊት ከጎፋ እስከ ሶዶ ሰባት ቀን ፈጅቶብኝ ነበር፣ አሁን ግን በሁለት ቀን ወደ ጎፋ ተመለስኩኝ። ጤንነቴ እጅግ በጣም ስለተሻለኝ ጥንካሬ አግኝቼ ቤቴን መሥራት ተያያዝኩኝና ወዲያውም ሠርቼ አጠናቀቅሁኝ።

ቤቱን ለመክደን ሣር ከማጨዴ በፊት ሌላ አዲስ ቤት የሠራ ሰው የቀድሞውን አሮጌ ሣር አፍርሶ ይጥል ነበር። ያ አሮጌ ሣር ጥላሸት የጠገበና ጥቀርሻ ቢሆንም፣ ለእኔ ቤት ግን ብዙና ተመጣጣኝ ነበር። በዚያ ሦስት ሜትር ስፋት በነበረው ቤት ውስጥ ለሦስት ዓመት ኖርን። በእጄ የሠራሁት ቤት ያ ነበር።

በእነዚያ በሦስት ዓመታት ውስጥ ወንጌልን ለመስበክ ብዙ መልካም አጋጣሚዎች ነበሩኝ። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ወደሚያርሱበት ቦታ እሄዳለሁ። አንዳንዶቹም ቤት ወደሚሠሩበት እሄድና ሥራ እያገዝኳቸው ከቆየሁ በኋላ አረፍ በምንልበት ጊዜ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት እመሰክርላቸዋለሁ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሰዎች ወደታመሙበት ቤት ሄጄ እጸልይላቸዋለሁ። አንዳንዶቹ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነናል ቢሉም፣ የተለወጠ ሕይወት አልነበራቸውም። ሌሎቹ ደግሞ አምነው ከተጠመቁ በኋላ መጠጣትና ብዙ ሚስቶች ለማግባት ስለሚፈልጉ ከእምነት መንገድ ወደ ኋላ ያፈገፍጋሉ። አንዳንድ ጊዜ በጣም ተስፋ እቆርጥና ወደ ቁጫ ለመመለስ እየተመኘሁ ዳግመኛም ወደ ጎፋ ዓይኖቼን ላላነሣ እፈልጋለሁ። ስለ ክርስትና ሕይወት ጥቂት ለሰሙ ሰዎች ወንጌልን ስንሰብክላቸው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑ እንነግራቸው ነበር።

እነርሱም፣ «በዓለም አዳኝ አንዴ አምነናል፣ እንዴት አሁን በኢየሱስ እናምናለን። ስለ ኢየሱስ የምታወራውን ስብከት አቁምና ወደ ወላይታ ተመለስ» ይሉኝ ነበር።

## ቀ ብ ር

አስቀድሜ እንደ ጠቀስኩት በእኛ አካባቢ ቀብር ላይ መገኘት በጣም ጠቃሚ ነው። ሰዎቻችን እያንዳንዱ ሞት ሥጋዊ ምክንያት እንዳለው ሁሉ መንፈሳዊ ምክንያትም አለው ብለው ያምናሉ። ከመጨረሻው ይልቅ የመጀመሪያውም የበለጠ ትርጉም ያለው ነው። በቀብር ላይ መገኘት

ማለት በእኛ በኩል ከምናምነው እምነት ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ይገልጻል። የባለቤቴ እኅት በቁጫ በሞተች ጊዜ ወደዚያ በተቻለኝ ፍጥነት መሄዱ ለእኔ አስፈላጊዬ ነበር፡፡ ጥቅሙ ለእኔ ከሚሆን ይልቅ ለመላው ቤተሰብ አባሎች አስፈላጊ ነበር። የሄድኩትም በማዜ ወንዝ በኩል ነበርና ወንዙ ሞልቶ ለመሻገር የማይሞከር ነበር። እንደዚያን ቀን በሕይወቴ ተከፍቼ አላውቅም። በወንዙ ዳር በትልቅ ቋጥኝ ድንጋይ ላይ ተቀምጬ እያለቀስኩና እየጸለይኩ የመኖሬን ተስፋ ቆርጬ ወደ ጌታ ለመሄድ ተዘጋጅቼ ነበር። ወደ ሥራዬ በምመለከትበት ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተለወጡት ጥቂት ሰዎች ይመስላሉ፣ ብዙዎች ተጠምቀዋል፤ ብዙዎችም ወደ ጸሎት ቤት ለጥቂት ጊዜ ይመጡና ቆይተውም ጌታን ክደው ወደ ኋላ ያፈገፍጋሉ።

«ታዲያ የዚህ ሁሉ ልፋት ጥቅም ምንድን ነው?» ብዬ ራሴን እጠይቅ ነበር።

በጤንነቴ በኩል ብዙም የተሻለኝ አይመስለኝም፡፡ ስራመድ ምንም ጥንካሬ አልነበረኝም፡፡ ሌላ የምሠራው ሥራ አልነበረኝም፡፡ ትንሽ በአካባቢው ዞር ዞር እልና ወደ ቤቴ ለመድረስ ሽቅብ እወጣ ነበር፡፡

ምናልባት በሽታዬ እንዲያገረሽብኝ ያደረገኝ በየቀኑ ጋራ ላይ የመውጣቴ ነገር ይመስለኛል። አንድ እሑድ ጧት በጸሎት ቤት ነፍሴና ሥጋዬ የተለየችኝ እስኪመስለኝ ድረስ ታመምኩ፡፡ ልቤ ሥራውን ያቆመና ነፍሴም ከሥጋዬ የተለየች ነበር የመሰለኝ። ለሃያ ቀናት በጣም ታምሜ በነበርኩበት ወቅት ብዙ ምእመናን ከተለያዩ ቦታዎች እየመጡ ይጸልዩልኝ ነበር። ወንጌልን ለመስበክ ያለኝን ከፍተኛ ምኞት ያውቁ ስለነበር እግዚአብሔር እንዲያድነኝና በቀሪውም ሕይወቴ ወንጌልን በተለያዩ ቦታዎች ለመስበክ እንድችልና እግዚአብሔር እንዲፈውሰኝ ምእመናን ተግተው ይጸልዩልኝ ነበር። በጸሎታቸውም ምክንያት ቀስ በቀስ እየተሻለኝ መጣ፡፡ ሙሉ ጥንካሬ አግኝቼም በባጋ አካባቢ የተለመደ ሥራዬን ቀጠልኩኝ።

ወንድሜ ዳንኤል በአካባቢው መሬት ተከራይቶ ለማረስ ወሰነ። ምክንያቱም ያን ጊዜ በርካታ ቁጥር ያላቸው ወንጌላውያን ወደዚያ አካባቢ ስለደረሱ ነበር፡፡ አብራን ትኖር የነበረችው እኅታችን አንድ ቀን በጠና ታመመች፡፡ ያለን ዘመዶቿ እኔና ባለቤቴ ብቻ ነበርንና እናስታምማት ጀመር። እንደዚህ ዓይነት አጋጣሚ ሲከሰት ቤተዘመድ ተሰባስቦ የሚያስታምም ሲሆን፣ እኛ ግን በአጠገባችን ማንም



ቤተዘመድ አልነበረንም፡፡ ጎረቤቶቻችን እንዲረዱንም አልጠየቅናቸውም።

እኅቴ በታመመችበት ወቅት የምንኖርበት አካባቢ ደጋማ በመሆኑ በጣም ይቀዝቅዝ ነበርና ተጨማሪ እንጨት ገዝተን በማንደድ ቤታችንን እንዳናሞቅ ገንዘብ አልነበረንም፡፡ አንድ የትልቅ ዛፍ ጉቶ አይቼ ነበርና የጉቶው ባለቤት ስጠይቀው ፈቀደልኝ፡፡ ያን ጉቶ ዙሪያውን እየቆፈርኩ በመፍለጥ ለሁለት ወር ሙሉ እንደ ልብ እያነደድን ቤታችን ለእኅቴ እንዲሞቅ አደረግን።

በእኛ አካባቢ ምንም ደሃ ቢሆን ሰው ሲሞት በአዲስ ጨርቅ ይከፈንና ይቀበራል። ገንዘብ ብታጣ እንኳን ተበድረህ የከፈን ጨርቅ መግዛት ይኖርብሃል፡፡ እኅቴ ሕመሟ እየጠናባት ለብዙ ጊዜ ልትኖር የማትችልበት ጊዜ እየተቃረበ መምጣቱን አስተውል ጀመር፡፡ ምንም መድኃኒት ልንገዛላት አልቻልንም፡፡ ምግብ መብላት አልቻለችም፡፡ ትንሽ ትንሽ ውኃ ብቻ ፉት ታደርጋለች፡፡ በሚቀጥሉት አንድና ሁለት ቀናት ውስጥ ልትሞት እንደምትችል እርግጠኞች ሆንን። ከተራራው ወረድ ብሎ ወደሚገኘው ሳውላ ወደሚባለው ከተማ አጠገብ ወደአለው ገበያ ሄጄ ለከፈን የሚሆን ጥቂት ሜትሮች ጨርቅ ለመግዛት ረዥም ጉዞ አደረግኩኝ፡፡ «ከኖረች ትኖራለች፡፡ ከሞተችም ትሞታለች፡፡ ምንም ማድረግ አልችልም፡፡» እያልኩ አወጣና አወርድ ጀመር።

ሸማ የሚባል ጨርቅ ገዝቼ ወደ ቤቴ በተመለስኩ ጊዜ ትንሽ እየተሻላት ነበር፡፡

ለሁለት ወር ሙሉ እየተሸከምናትና እያገላበጥናት ስለነበር አሁን እየተሻላት ሲመጣ እኛም ከፍተኛ ዕረፍት አገኘን። አሁን ደግሜ ስብከቴን ቀጠልኩ፡፡ ከባጋ ይልቅ አገልግሎቴ በካሪዛ እያደገልኝ በመምጣቱ በዚያ ቤት ሠርቼ ለመዛወር አሰብኩ፡፡ ለአጨዳ ያልደረሰውን ሰብላችንን ትተን ወደ ጎፋ ብንመጣም በቁጫ ያለን መሬታችን በእኛ ይዞታ ሥር ስለሆነ እግዚአብሔር ይመስገን ይህም ማለት በማንኛውም ጊዜ ከቁጫ ገንዘብ ወይም ምግብ ለማምጣት ስለምንችል ጊዜው ተጠብቆ ከወላይታ ለማይሰጠን አነስተኛ ገንዘብ ማካካሻ ሆኖን ነበር። የባለቤቴ እናት መሞታቸውን ስንሰማ ወንድሜና እኔ ወደ ቁጫ አፋጣኝ ጉዞ ለማድረግ ወሰንን።

በአገራችን አንዳንድ ወሬ በጣም ይዘገያል፡፡ ሆኖም በቤተሰብ ውስጥ ሞት ሲከሠት ፈጥኖ መስማት በጣም አስፈላጊ ነበር፡፡ ወሬው

ከሰው ወደ ሰው እየተላለፈ ይሰራጭ ስለነበር፣ በወቅቱ ከስልክ ያላነሰ ፍጥነት ነበረው።

ጎፋን ከቁጫ ስለሚለየው ስለ ማዜ ወንዝ አስቀድሜ ገልጬላችሁ ነበር። ሌላ ደግሞ ዘንቴ የሚባል ትልቅ ወንዝ ነበር። ወሬው የደረሰን በዝናብ ወቅት ቢሆንም፣ ወደ ቁጫ ለመጓዝ ልዩ ጥረት ማድረግ ነበረብን። ተራራማውንና ሰንሰለታማውን መንገድ ተጉዘን ወደ ማዜ ወንዝ ለመድረስ ሁለት ቀን ፈጀብን። ተመሳሳይ ታሪክ የሆነብን ወንዙ ከፍታው እጅግ በጣም የጨመረ በመሆኑ ለመሻገር የሚታሰብ አልነበረም። ተራራውን ወጥተን ወደ ቤታችን መመለስ ነበረብን። በባጋ ቤታችንን የምትጠብቅልን እኅቴ ነበረች። ባለቤቴ ድርስ እርጉዝ ስለነበረች በካሪዛ ጓደኞቼ ዘንድ ትቼአታለሁ።

ካሪዛ ማለት አስቀድመን ከቁጫ ወደ ጎፋ በመጣን ጊዜ ችግር አጋጥሞን የነበረበት ስፍራ ነው። በዚህ ቦታ ነው እንግዲህ የአምስት ሜትር ስፋት ያለውን ቤት ለመሥራት የወሰንኩት። በአካባቢው ብዙ ክርስቲያኖች ካለመኖራቸውም ባሻገር፣ ጥቂት አማኞች ደግሞ በእምነታቸው ያልጠነከሩ ነበሩ። ነገር ግን እኛ ወደ መንደራቸው እንድንሄድላቸው ይፈልጉ ነበር። እዚያም ስንደርስ ቤት በመሥራት በጣም አገዙን። ወቅቱ የበጋ ወራት ስለሆነ በቂ ምግብ አይገኝም ነበር። የመንግሥት ባለሥልጣኖችና የመሬት ከበርቴዎች ክርስቲያኖችን ያስፈራሩ ስለነበር የበለጠ ችግር እንደሚጠብቀን እናውቃለን።

በእኛ አካባቢ የቤት ጣራ ነቅሎ መሸጥ የሚቻል ሲሆን፣ ከንችና የቤት መክደኛ ሣርም እንዲሁ ወደ ሌላ አካባቢ ከሚዛወር ሰው መግዛት ይቻል ነበር። የላይኛውን ጣራ እንዳለ ነቅለን እንሸከምና ወደ ሌላ ስፍራ በመውሰድ ለአዲሱ ቤት ጣራ በማድረግ እንሠራለን። በዚያን ጊዜ ሰዎች ቤታቸውን በየትኛው ቦታ እንደሚሠሩ ለመወሰን እንግዳ የሆነ እምነት ነበራቸው። በአካባቢው በሽታ ወይም ሞት ቢከሠት ወይም ከብቶች ሲሞቱ ሰዎች ሄደው ጠንቋይን ያማክሩ ነበር።

ጠንቋዩም፣ «ቤትህን የሠራኸው በማይሆን ቦታ ስለሆነ መጥፎ ዕድል ሊመጣብህ የቻለው ለዚህ ነው» ይላል፤ ወይም፣ «የቤትህ በር ወደ መጥፎ አቅጣጫ ዞሮ ስለተሠራ ነው» ይላቸዋል።

ሰዎቹም ወዲያው ቤታቸውን አፍርሰው በመንቀል ወደ ሌላ ቦታ ያዛውራሉ።



በዚሁ ምክንያት አንድ አዲስ ቤት ሲሠራ የአሮጌውን ቤት ንቃይ የተጠናቀቀውን የቤት ጣራ ገዝቼ ቤቴን ሠራሁበት። ጉድጓዶች ቆፈርን፣ የማዕዘን እንጨትና እንዲሁም ግድግዳ አቆምን፣ የማዕዘን እንጨቱን በጉድጓድ ወስጥ አቁመን ከጣራው ጋር ጠፍረን አሠርነው። የጣራውን ሥራ ለማሠር ጠንካራ ገመድ እንጠቀማለን። ቤቱ በጠቅላላው ሲሠራ አንድ ሚስማር እንኳን አልተጠቀምንም ነበር።

የመካከለኛው ማዕዘን በሚገባው ቦታ ተቀምጧል፤ ቤቱም በሣር ሊከደን ተዘጋጅቷል። ስፋቱ አምስት ሜትር ነው። ከቀድሞው ሦስት ሜትር ስፋት ከነበረው ቤታችን ስናወዳድረው ይሄ ትልቅ ቤት ሆነልን።

ከአሮጌው ቤታችን ጣራ ሣሩን አነሣንና የቀርከሃ መቃኖቹን ጭምር ወደ አዲሱ ቤታችን ጣራ ወስደን ገጠምን።

አዲሱን ቤታችንን ስንሠራ በነበርንበት ወቅት፣ ባለቤቴ ሰብላችንን ከሚበላ አውሬ ለመጠበቅ ወደ ቦጋ ተመለሰች። እኅቴ ከእኔ ጋር ቆየች። ወንድሚም በአንዱ ማኅበር ሽማግሌና ወንጌላዊ እንዲሆንላቸው ስለተጠየቀ ለአጭር ጊዜ ወደዚያ ሄዷል። ስለዚህም ነበር አደጋው በተከሠተ ጊዜ ብቻዬን የነበርኩት።

በተለይም በዚያ ሳምንት መጨረሻ ውስጥ የጥምቀት ሥነ ሥርዓትን ለማከናወን ቀጠሮ ይዘን ነበር። ከዚህም የተነሣ ቤቱን ለመጨረስ በጣም እንጣደፍ ስለነበር የቀርከሃ ጣራ ተሸክመን በምንሄድበት ወቅት አንዱ አደናቀፈንና ሚዛናችንን ስተን የተሸከምነውን ለቀቅን። በዚያ የአጋጣሚ ክስተት ውስጥ እኔ ተደናቅፌ ወደቅሁና የተሸከምነው የቤቱ ጣራ እንዳለ በጀርባዬ ላይ ወደቀ ሌሎች ሰዎች ተጋግዘው ከላዬ ሊያነሡልኝ ቻሉ እንጂ ብሞት እንኳን እመኝ ነበር። ወዲያው ሰውነቴ ከፍተኛ ትኩሳት ለቀቀብኝ። ከራስ እስከ እግሬ ድረስ ከፉኛ ያንቀጠቅጠኝ ነበር። ሰውነቴም በሙሉ ውኃ ሆነ። ሌሊቱን በሙሉ ውኃ እየጠጣሁ አሳለፍኩኝ። ብዙ ውኃ ብጠጣም እንኳን የሰውነቴ ትኩሳት አልቀነሰልኝ ም። በጣም ከመታመሜ የተነሣ ከእግዲህ በሕይወት የምኖር አልመሰለኝም ነበርና ወደ እግዚአብሔር እቤት ማለት ጀመርኩ።

«አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ፣ እዚህ ለመሥራት የመጣሁት ያንተ ፈቃድ ስለሆነ ነው። ወደዚህ ስፍራ የጠራኸኝ አንተ ነህ። አሁን ደግሞ እዚህ የተገኘሁት እነዚህን ሰዎች ለማጥመቅ ነው። ለምን ይህ ሁሉ

ይደርስብኛል? እኔ እንድሞት ያንተ ዓላማ ከሆነ መልካም ነው፣ ለመሞት እፈልጋለሁ» አልኩኝ።

እንዴት ልታመም እችላለሁ? ደመወዛችን ከወላይታ ሶዶ የሚመጣልን የሽማግሌዎች መማክርት ገንዘብ ሲኖራቸውና ሲልኩልን ብቻ ነው። ምንም ሳንቀበል ስንት ወር ልንቆይ እንደምንችል በፍጹም አናውቅም:: አንድ ሰው ከመካከላችን ገፋፍተን ወደ ወላይታ ሶዶ ገንዘብ ሊያመጣልን ብንልክ ብዙውን ጊዜ እዚያ ለመድረስ በእግሩ አምስት ቀን ይወስድበታል። በተጨማሪም በአንድነት የሚጓዙ ሲራራ ነጋዴዎችን መጠበቅ የሚገባው ሲሆን፣ ከአህዮቻቸውና ከበቅሎቻቸው እኩል ለመሮጥ በተለይም በበጋ ወቅት እጅግ አስቸጋሪና ተከታትለውም ሲጓዙ ውኃ ለማግኘት አዳጋች ነበር። እንኳን አደጋ ተጨምሮበት ሕይወት ለሁላችንም እንዲሁ በጣም የከፋ ነበር።

ያን ጊዜ ለመኖር አንዴ እንኳን አልጸለይኩም፣ እንዲያውም ይሻለኛል ብዬም አላሰብኩም ነበር። እጸልይበት የነበረው ነገር ቢኖር እነዚያን ሰዎች በተመለከተ እግዚአብሔር ዓላማውን እንዲገልጽ ብቻ ነው:: በጉዳቴ በጣም ሕመም ይሰማኝ ነበርና ለረዥም ጊዜ አላገገምኩም። ከቀን ወደ ቀን የተሻለ ጤንነት አይሰማኝም ነበር።

አንድ አሳብ መጣልኝ፤ ምናልባት ወደ ትውልድ አገሬ ሄጄ ለተወሰነ ጊዜ መቆየት አለብኝ ብዬ አስቤ ነበር:: ግን እንዳልሄድም በጉዳዩ እጸልይበት ነበር። ወደ ቁጫ (ትውልድ አገሬ) በምመለስበት ጊዜ የጎፋ ሰዎች፣ «ወደ አገሩ የተመለሰበት ምክንያት እምነቱን ስላልተቀበልን ነው» ይሉኛል፤ መታመሜንም ይረሱታል ብዬ አሰብኩኝ ::

ጓደኞቼም፣ «እዚህ ተቀምጠህ እንዲህ ለምን ትሠቃያለህ? በእርግጥ አሁን እዚህ የምትሆንበት ትክክለኛ ጊዜ አይደለም:: እነዚህ ሰዎችም በክርስቶስ ለማመን የተዘጋጁ አይደሉም:: በትውልድ አገርህ በቁጫ መሬትና የእርሻ ሰብል አለህ:: ስለዚህ ለተወሰነ ጊዜ ወደ ቁጫ ብትመለስ የተሻለ ነው:: እዚህ ስላለው እርሻህ የምትጨነቅ ከሆነ እኛ እንጠብቅልሃለን። ወይንም ልጆችህን ወይም ወንድምህንና እኅትህን እዚሁ ሰብልህን እንዲጠብቁልህ ትተህ መሄድ ትችላለህ። ወደ ቁጫ ብትመለስ ለጤናህ መልካም እንደሚሆን አይመስልህም?» አሉኝ::

አሳባቸውን በልቤ ከተቀበልኩ በኋላ:: ጓደኞቼ የሚሉኝ ሁሉ እውነት እንደሆነ ተረዳሁ። ያቀረቡልኝ ምክንያት ግን በቂ እንዳልሆነ



ነገርኳቸው:: «ቁጫን ተሰናብቼ የመጣሁት ወንጌልን ለመስበክ ነው:: እንዴት አድርጌ ወደ ትውልድ አገሬ እመለሳለሁ?»

«ጌታ ሆይ፣ ወደ ትውልድ አገሬ ከምሄድ እዚሁ ልሙት እባክህ ውሰደኝ ብዬ ጸለይኩ::

«እንዲያውም ወደ ቁጫ ከምሄድ ወደ መንግሥተ ሰማያት ብሄድ ይሻለኛል:: በተጨማሪም፣ «እኔ ለራሴ ይህን ቦታ አሁን ብለቅ፣ ሰዎች በእኔ ወንጌላዊነት ተስፋ ይቆርጡና በሌላውም እንዲሁ ተስፋ የሚቆርጡ ይሆናሉ» አልኩ::

በዚያን ጊዜ፣ ለሁለተኛ ጊዜ ስታመም አሁንም ዳግመኛ አቤቱታ ለእግዚአብሔር አቀረብኩ:- ብዙ ሰዎች እንዲያምኑ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ አደርጋለሁ። መሞት አስፈላጊዬም ከሆነ ለመሞትም ፈቃደኛ ነኝ።

## በሞት አፋፍ ላይ

ይህ ከእኔ ታሪክ ፊት ለፊት የሚሄድ ነገር ነው። በቤቱ ላይ ጣራውን እየሠራን ውለናል:: ማታ ደግሞ የጥምቀት ሥነ ሥርዓት ለማከናወን ዕቅድ ይዘናል። የጥምቀትን ሥነ ሥርዓት ማታ ለማድረግ የፈለግንበት ምክንያት የአካባቢው ባለ ሥልጣኖች ስለሚያስፈራሩን ነው:: እኔ በጣም እየታመምኩ ከመሆኔም በላይ፣ ከፍተኛ ራስ ምታትና ትኩሳት ይዞኛል:: እንደዚህ ሆኜ አሥር ሰዎችን ወደምናጠምቅበት የማጥመቂያ ቦታ ሄድኩኝ::

በጥምቀቱ ቦታ ትኩሳቴ በጣም አየለብኝ:: በደረቴ እየተሳብኩኝ በአካባቢው ወደሚገኝ ቤት ደረስኩና በመለል ላይ ለመተኛት ወደቅኩኝ :: በሚቀጥለው ቀን አቶ አንድሪ ሪጋሮ የሚባል ሰው እንደ መሸከም አድርጎኝ የላ ወደሚባል ቦታ አደረሰኝ:: በወቅቱ ሕሊናዬን ስቼ ስለነበር ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሲያንቀሳቅሱኝ አላውቅም ነበር። ሰዎች ምን እያደረጉኝ እንዳሉና እኔም የት ቦታ እንዳለሁ አላስታውስም ነበር::

አዲስ ክርስቲያን ወደነበረች አንዲት ሴትዮ ቤት ወሰዱኝ:: ሲትዮዋም በእንግድነት ተቀብላ ልታስተናግደኝና ልትንከባከበኝ በጣም ደስ አላት:: ወደዚህች ሴትዮ ቤት ባደረሱኝ ጊዜ የት እንዳለሁ በትክክል አላስታውስም ነበር:: ምን እንደማደርግም አላውቅም ነበር።

በዚያ ቤት ውስጥ የእናቴ ዕድሜ ያህል የነበሩቸው ሽማግሌና አሮጊት ነበሩ:: ታምሜ በነበርኩበት ቦታ ሆኜ ስለ ጌታ ኢየሱስ አዳኝነት ለአሮጊቷ ነገርኳቸው::

አንዳንድ ሰዎች ግን፣ «እርሳቸው ለራሳቸው ማየት የተሳናቸው አሮጊት ናቸው፣ ለምን ታስጨንቃቸዋለህ» ይሉኝ ነበር።

አሮጊቷም መልሰው፣ «እባክህ ልጄ መሐሪ እንዲህ ዓይነት ነገር ለምን ትናገረኛለህ? ሕይወቴ እያለቀ መሆኑን አታይም? ዓይኔም ማየት አይችልም:: ሞቴን ብቻ እየጠበቅኩኝ ነኝ:: ስእኔ ለምን ትሰብከኛለህ?»አሉኝ::

እኔም መልሼ፣ «በኢየሱስ ክርስቶስ ቢያምኑ፣ የዘላለም ሕይወት ተካፋይ ይሆናሉ:: ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያው ነው:: ለዘለዓለምም የሚኖር ነው:: የእርስዎ አካል ወደ አፈር ቢመለስም፣ ጌታ ኢየሱስ ግን አዲስ ሕይወት ይሰጥዎታል» ስላቸው።

«ይህ የምትነግረኝ እውነት ነው? መሐሪ፣ እውነትህን ነው?» እያሉ ደጋግመው ጠየቁኝ::

እኔም፣ «አዎን፣ እውነት ነው» ብዬ አረጋገጥኩላቸው:: «በሥጋዊ አካል እንሞታለን፣ ነገር ግን በክርስቶስ አዲስ ሕይወት እናገኛለን:: ሥጋዊው ሞት አዲሱን ሕይወት ለማግኘት የምንሸጋገርበት ነው::»

ለጥቂት ጊዜ ውይይታችንን ቀጠልን:: አሮጊቷም ብዙ ጥያቄዎችን ጠየቁኝ:: እኔም መልስ ሰጠኋቸው:: በመጨረሻም እንዲህ አልኳቸው፣ « አሁን እጅዎን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ዝግጁ ነዎት?» አልኳቸው::

እርሳቸውም «እሺ፣ ሰይጣንን ክጃለሁ:: ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኜ አድርጌ ተቀብዬዋለሁ» እያሉ ቃሉን በመደጋገም ሁለቱንም የገረጡ ክንዶቻቸውን ወደ ላይ አነሡ።

«ዳግመኛ ጌታዬን አልክደውም» ይበሉ አልኳቸው:: ምንም ሳያመነቱ ቃሉን ደገሙልኝ::

«የኢየሱስን መስቀል እሸከማለሁ:: ወደሚመራኝ ሁሉ እከተለዋለሁ» ይበሉ አልኳቸው:: ይህንንም ደገሙልኝ።

«ወደ አሮጌ ሕይወትዎ ላለመመለስ ወስነዋል? ሳያቋርጡ ወደ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይጸልያሉ? ዳግመኛ ወደ ጠንቋይ ቤት አይሄዱም?» ሁሉንም ጥያቄ በመስማማት መለሱልኝ::

«አሁን የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ መሆንዎን ለሌሎች ሰዎች ይነግራሉ?» አልኳቸው:: «አዎን፣ እነግራቸዋለሁ» ብለው መለሱልኝ::

እኔም «ሕይወትዎን የሰጠዎት እግዚአብሔር ብርታትን ይስጥዎት» አልኳቸው::



እርሳቸውም፣ «አሜን! አሜን!» አሉ:: ከዚያ በኋላም እኔ ራሴን ሳትኩኝ።

ጓደኞዬ ኢርጋቶ መጥቶ ያስታምመኝ ነበር:: እውነት ይሁን ውሸት ባለውቅም ለአርባ ቀን ሙሉ ራስህን አታውቅም ብሎ ጓደኛዬ ነግሮኛል። የት እንዳለሁ ማስታወስ እንደ ጀመርኩ (ወደ አዕምሮዬ እንደ ተመለስኩ) አቶ ዓለሙ ሊጎበኘን መጣ:: ምን ያህል ታምሜ እንደ ከረምኩ ተመለከተኝ:: ቆሞም በቋንቋችን ሳይሆን በአማርኛ ጸለየልኝ:: እንባ ከዓይኑ እንደ ውኃ ይወርድ ነበር:: ያን ጊዜ ነበር ወደ ልቤ የተመለስኩት።

«ጋሼ»፣ አልኩት ጎርነን ባለ ድምፄ የአቶ ዓለሙን ትኩረት እየሳብኩኝ::

እርሱም፣ «አቤት» አለኝ::

«ለምን እንደዚህ እያለቀስክ ትጸልያለህ?» ብዬ ጠየቅኩት:: እርሱም «እግዚአብሔር እየተወን ነው? ለምንድን ነው የሚወስድህ? ያለአንተ እኛ ብቻችንን ምን ልንሠራ ነው? አትለየን:: የእግዚአብሔር ቃል የበለጠ እንድታስተምረን እንፈልጋለን» አለኝና እንደገና ዓይኑ በእንባ ተሞላ::

እኔም መልሼ፣ «ጋሼ፣ እንደዚህ አትጸልይ» ስለው:: «ለምን?» አለና ጠየቀኝ::

«ምክንያቱም ጸሎትህ ተመልሶልሃል:: ዛሬ የመጣኸው እኔ በሕመሜ ምክንያት ወደ አገሬ እንዳልመለስ ልትጸልይልኝ ነው። እኔም ወደ አገሬ እንዳልመለስ ለእግዚአብሔር አቤቱታ አቅርቤአለሁ። ወደ ቂጫ ከምመለስ እዚሁ ብሞት ይሻለኛል:: ከሕመሜ የተነሣ ወደ ትውልድ አገሬ ለመመለስ አልፈልግም። አሁን ጸሎትህ ተመልሶልሃል:: አቤቱታዬም ተፈጽሞልኛል:: አሁን ግን ልሞት ነው:: እንድድን እንኳን አትጸልይልኝ።»

ምን እናገር እንደነበር ብዙውን አላውቅም:: አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ሲናገሩ እሰማቸዋለሁ። አንዳንድ ጊዜ እበላስሁ፣ እጠጣስሁ:: ጓደኞቼ ወደ ሶዶ ሄደውም ከዶክተር ባርሎው መድኃኒት አምጥተውልኝ አስውጠውኛል፣ ምናልባትም ረድተውኛል::

ከከባድ ሕመሜ የተነሣ አልተነሣሁምና ቀኝ ጎኔ እያበጠብኝ ነበር ። የትኩሳቴ መጠን የሰውነቴን ቆዳ የለወጠው ከመሆኑም በላይ፣ ከንፈሮቼ

እየተሳሳጡ ቅርፊት ይነግባቸው ጀመር። በመጨረሻ ግን ዳንኩና ወደ ስብከቴ ተመለስኩኝ። እግዚአብሔር ይመስገን።

## ችግሩ ማለቂያ የሌለው ይመስላል!

ትልቅ ቤት በመሥራታችን በጣም ተደስተናል። ቢሆንም ከአካባቢው ባለሥልጣኖችና ከመሬት ከበርቴዎች የሚመጡብን ችግሮች እያየሉና እየጨመሩ መጥተዋል። ወደ አዲስ አበባ ሄደን ከበላይ ያመጣነው ወረቀት ሕግን እስካልተቃወሙ ድረስ መጽሐፍ ቅዱስን ማስተማር ይችላሉ በፈለጉትም መንገድ እግዚአብሔርን ማምለክ ይችላሉ የሚል ነበር። ያ ወረቀት ግን የሚደርስብንን ችግር አላቃለለልንም።

አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች በዱላ ይደበደቡ ነበር፤ አንዳንድ ጊዜም ያለ ምክንያት ይታሠሩና ወደ እስር ቤት ይገባሉ። ይሄ ደግሞ በተለይ የሚበረታው የጥምቀት ሥርዓት ልናስፈጽም መሆኑን የማያምኑ ሰዎች በሚሰሙበት ጊዜ ነበር።

በጎፋ ሥራ የጀመርነው ከ1941 -1942 ዓ.ም ላይ ነበር። እጅግ ብዙ ሰዎች በእምነታቸው ምክንያት ለእስር ተዳርገዋል። በአንድ ቦታ አሥራ አንድ ሰዎች ለሁለት ወር በቡልቂ ከተማ ታሥረዋል። በዚህን ጊዜ ሳልታሰር በመቅረቴ በእሥር ላይ የነበሩትን ክርስቲያኖች ለመርዳት ችያለሁ።

እነዚያ ክርስቲያኖች ወደ ቡልቂ ተወስደው ስለታሠሩ ከርቀቱ የተነሣ ቤተሰቦቻቸው ምግብ ለማቀበል አልቻሉም ነበር። አንዳንድ ጊዜ ገንዘብ አምጥተው ለእኔ ይሰጡኝ ነበር። ብዙውን ጊዜ አህያ እየነዳሁ ሦስት ቀን ሙሉ ተጉዤ ከገበያ በቆሎ ገዝቼ ካመጣሁ በኋላ፣ እኅቴ ፈጭታ፣ ቂጣ ጋግራ፣ ጎመንም አዘጋጅታ ታቀርብና ባለቤቴ ደግሞ በጀርባዋ ለእሥረኞቹ ታደርስላቸዋለች። ይህ ከባድ ቢመስልም ብዙ ክርስቲያኖችም ረድተውናል።

የባለሥልጣኖቹ ዋና ዓላማ ፀረ ማኅበራዊ ነው የሚሉትን እንቅስቃሴ ለማስቆም ነበር። አሳዳጆቻችን ክርስቲያን ከመሆናችን በፊት የኖርነውን ሕይወት ብቻ እንድንኖር ይፈልጋሉ። በእርግጥ፣ ያንን በፍጹም አናደርገውም።

በ1943 ዓ.ም አካባቢ እንደ ወንጀለኞች የምንቆጠርበት ምንም ምክንያት ሊኖር እንደማይችል ተረዳን። በዚህም ምክንያት ነበር በጎፋ



የነበሩት ክርስቲያኖች እኔንና አቶ ዓለሙን ወደ አዲስ አበባ ለመላክና የማምለክ ነጻነት እንዳለን የሚያረጋግጥ ወረቀት እንድናመጣ የወሰኑት። ያ ለእኔ ወደ አዲስ አበባ ስሄድ የመጀመሪያዬ ጉዞ ነበርና የፈለግነውን ወረቀት ለማግኘት እግዚአብሔር ረድቶን ይዘን ተመለስን። ነገር ግን አስቀድሜ እንደገለጽኩት፣ ነገሮች አልተሻሻሉልንም፣ ችግሮችም አልቀለሉልንም።

አንድ ቀን በጸሎት ቤት ስብሰባ ላይ እንደ ነበርኩ፣ አንድ መልእክተኛ መጥቶ፣ «የሆኑ ሰዎች መጥተህ የወንጌልን መልእክት እንድትነግራቸው ይፈልጋሉ። እኔም ልጠራህ ተልኬ መጥቼአለሁ» ብሎ ተናገረኝ።

ለምን ወደ ጸሎት ቤታችን መጥተው ለመስማት እንዳልፈለጉ ባይገባኝም፣ ከመልእክተኛው ጋር ለመሄድ ራሴን አሳምኜ ተነሣሁ። ወደ ተባለው ቦታ ወዲያው እንደ ደረስን ለባለሥልጣኖቹ ምልክት ሰጣቸው። ወዲያውም ይጠባበቁ የነበሩት ባለሥልጣኖች ተኰሳድጉደው ወጡ።

«በየገጠሩ እየተዘዋወረ የሚሰብከው ወንጌላዊ ይህ ነው» አላቸው።

ሁልጊዜ ሰዎች እውነተኛ ሥራዬን እየገለጹ ሲከሱኝ ደስታ ይሰማኛል። በዚህ ጊዜ ለሦስት ሳምንት ብቻ አሥረው ለቀቁኝ። አንዳንድ ጊዜ ማስፈራራታቸው ሰዎችን ተስፋ የሚያስቆርጥ ቢሆንም፣ አንዳንድ ጊዜ ግን የሚጎዳቸው አይሆንም። በዚህን ጊዜ ብዙ ክርስቲያኖች ስደቱንና ማስፈራራታቸውን አልፈሩም ፤ እንዲያውም እጅግ ብዙ ሰዎች ወንጌልን ለመስማት ይፈልጉ ነበር። ብዙ ሰዎችም ማመን ጀመሩ።

እኔ ደግሞ ያን ጊዜ ለባጋ ቅርብ በሆነው ዳዳ በሚባለው ቦታ እሰብክ ነበር። ጸሎት ቤት ተሠርቶ በዛ ያሉ ሰዎች እየተሰበሰቡ በየእሁዱ ለማምለክ ይመጡ ነበር። በተጨማሪም አይከኔ ወደሚባል ቦታ ሄጄ ማስተማርን ቀጠልኩኝ። እዚያም የጸሎት ቤት ተሠርቷል። በቃንቾ ሄደን መስበክ እንደ ጀመርን ችግርም አብሮ ተቀሰቀሰ። ከስደት ይልቅ ቃሉ ተስፋፍቶ እዚያም የጸሎት ቤት ተመሠረተ። ከዚያም ቤኔ ወደሚባል ቦታ ተንቀሳቀስኩ፣ ከዚያም መሎ ወደሚባለው ቦታ በመሄድ በእነዚህ ቦታዎች ሁሉ ለቡድንና ለግለሰቦች ወንጌልን በሰፊው ለመመስከር ችያለሁ። ጌታም ቃሉን ባርኮ ብዙ ሕዝብ ወደ ደኅንነት መጡ።

በ1945 ዓ.ም ወይም በ1946 ዓ.ም ውስጥ ናና የሚባል ወንጌላዊ ወደ ጎፋ ደረሰ። ያኔ በአሪ አካባቢ አሥራ ሁለት ማኅበራት እንደነበሩ ያስታውስ ነበር።

## ዳግም መታሠር

በእነዚያ በተለያዩ ቦታዎች እየተዘዋወርኩ በአገልግሎቴ ሰፊ ተሳትፎ እያሳየሁ በነበርሁበት ወቅት እንደገና ታመምኩኝ። በዚህን ጊዜ መጥፎ በሽታ በደረቴ ይሰማኝ ጀመር:: ዶክተር ባርሎው በወላይታ ሶዶ ኤስ ኣይ ኤም ሆስፒታል እንዳሉ አውቅ ነበር:: ስለዚህ በቀጥታ ወደ ሶዶ ሄጄ የእርሳቸውን ምክር ለመጠየቅ ወሰንኩኝ። በተጨማሪም በ1951 ዓ.ም የተጀመረውን የኤስ ኣይ ኤም ሥራን ለማስፋት ሚስተር ዲክ ማክሊላን የሚባሉ ሚስዮናዊ ወደ ቡልቂ የመጡበትም ወቅት ነበር። እኚህ ሰው ብዙውን ጊዜ በመኻንገር የሚረዱን ነበሩ።

ይሁንና ወደ ሶዶ ከመኼዜ በፊት ዳግመኛ ታሠርኩኝ:: ወደ ወህኒ ከስገቡኝ በኋላ የዚያ አካባቢ ዳኛ እስኪመጡ ድረስ ታሥሬ እንደምቆይም ነገሩኝ። እንደ አጋጣሚ የአውራጃ አስተዳደር ጸሐፊ የነበረው ሰው ዳኛ ነኝ እያለም ያስመስላል:: ይህ ሰው ለገንዘብ የነበረው ፍላጎት በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ብዙ ጉቦ ቢሰጡትም አሁንም የበለጠ ገንዘብ ይፈልግ ነበር።

«መሐሪ፣ ለምንድን ነው የታሠርከው? እዚህ ታሥረህ መቆየት አይኖርብህም:: አሁኑኑ ተፈትተህ ወደ ቤት መሄድ ቀላል ነው» አለኝ በየነ አብርሃም የተባለው ዳኛ።

ምን እንደ ፈለገ ስለማውቅ ለንግግሩ ትኩረትና ቦታ አልሰጠሁትም::

«ማድረግ ያለብህ ምንድን ነው መሰለህ:: ለእኔ ስድስት ብር፣ ለአስተዳደሪው ስድስት ብር፣ በድምሩ አሥራ ሁለት ብር ከሰጠኸኝ ወደ ቤትህ መሄድ ትችላለህ» አለኝ።

«በፍጹም የማይቻል ነው! ጉቦ በፍጹም አልሰጥህም፣ አንዳች ነገር አልከፍልህም» ብዬ መለስኩለት::

«በእኔ በኩል መልካም ነው» አለኝ። በዝቅተኛ ድምጽ ቁጣውን ለመደበቅ እየሞከረ:: «ካልከፈልክ እንግዲህ እዚችው ትኖራለህ» አለኝ::



«ለእኔ ጥሩ ነው» አልኩት:: «ያለምንም ቅድመ ሁኔታ (ማረጋገጫ) ከእሥር ለመፈታት ለአንተ ጉቦ ልሰጥህ? ዳግመኛ እንደዚህ ዓይነት ጥያቄ ባታነሣብኝ ይሻላል» ብዬ ቁርጥ ያለ ተመሳሳይ መልስ ሰጠሁት።

ለራሴ ጠላት እያበጀሁ እንደነበር አውቅ ነበርና ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብኝ ተገንዝቤአለሁ:: ሰውየው የሥነ ልቡና ውጊያ መዋጋት ተያነው:: እኔም አሸነፍኩ:: እንዳሸነፍኩት በተረዳ ጊዜ ሊደበድበኝ ጥቃቅን ምክንያቶች ይፈልግብኝ ነበር:: አሁንም ምክንያት አጣ፣ በድጋሚ አሸነፍኩት:: ውይይታችንን ማንም አልሰማም ነበር።

በከተማ ውስጥ ዋልዳ መንታሶ የሚባል እኔ በታሰርኩበት ፖሊስ ጣቢያ ዘበኛ የነበረ ሰው ነበር። ያን ጊዜ እኔ ስላልተፈረደብኝ «ትልቁ ወህኒ ቤት» በሚባለው አልታሠርኩም። አንዳንድ ቦታ ወህኒ ቤት ሲባል ሌላኛው ፖሊስ ጣቢያ ይባላል። በፖሊስ ጣቢያ ሁኔታው በጣም የከፋ ነበር። ይህ ወታደር ሁልጊዜ እንደ ጓደኛ ይቀርበኛል። ነገር ግን ብዙም ሳልቆይ ወደ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ሊያስገባኝ እንደሚችል ተረዳሁ።

በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ በቆየሁ ጊዜ፣ የተወሰኑ እሥረኞችም እዚያው ነበሩ:: አንዳንዶቹ ነፍስ ገዳዮች ነበሩ:: እኔም እዚያው ፊደልን መጻፍና ማንበብ እንዳስተምራቸው ተፈቀደልኝ:: በዚያውም እሰብክላቸው ነበር።

አንድ ቀን ንባብ እያስተማርኳቸው በነበርኩበት ወቅት ይኸው ወታደር ወደ እኔ ቀርቦ፣ «የማቴዎስ አባት ለመሆኑ ዛሬ ምግብ ቀምሰዋል?» አለኝ:: በፖሊስ ጣቢያ እሥረኞችን መንግሥት አይቀልብም፣ ምግቦቻቸውን የሚያቀርቡላቸው ቤተሰቦቻቸው ናቸው። «ቤተሰቦቼ ገና ምግብ አላመጡልኝም» ብዬ መለስኩለት።

እሥራት ሲመጣ ምንጊዜም ከታሠሩት ሰዎች ይበልጥ ችግሩ የሚበዛው በቤተሰቦቻቸው ላይ ነው። ቤተሰቦቻቸው ለታሣሪዎቹ በየቀኑ ምግብ ማመላለስ ነበረባቸው::

«ይህ ገንዘብ ሌላ ሰው የላከልህ ነው ተቀበልና ሄደህ ዳቦና ሻይ ግዛበት» አለኝ።

በርግጥ ለእኔ የሚለኝ አዲስ ነገር አይደለም:: ሰዎች ብዙውን ጊዜ ለወህኒ ቤት ዘበኞች ገንዘብ ይሰጣሉ:: ይህ ከተደረገላቸው እሥረኞቹ («አደገኛ» ወንጀለኞች የተባሉትም እንኳን ቢሆን) ወደ ከተማ ወጣ ብለው ተናፍሰው እንዲመለሱ ዘበኞቹ ሊፈቅዱላቸው ይችላሉ።

«እኔ አልወጣም:: ከወጣሁኝ ችግር ሊመጣብኝ ስለሚችል አልወጣም አልኩኝ። ታማሪዎቼን ፊደልና እንዲሁም መጻፍና ማንበብ አስተምራቸዋለሁ። እኔም ዘበኛውን፣ እባክህ እኛን ተወንና ሂድልን» አልኩት::

እርሱም መልሶ፣ «ዛሬ እዚህ ማንም የለም:: የጣቢያው ኃላፊ እኔ ብቻዬን ነኝ:: ቀን ሙሉ እንኳን ብትውሉ ማንም የሚያውቅ የለም:: ወደ ከተማ ወረድ ብላችሁ ሻይና ዳቦ በልታችሁ ለመመለስ ግማሽ ሰዓት ብቻ ይፈጅባችኋል» እያለ በላላ ድምፅ ሊያሳምነን ይሞክር ነበር።

«ገንዘቡን ለመቀበል ካልፈለግክ፣ እኔ ግድ የለኝም:: ለሌላ እሥረኛ ልሰጥ እችላለሁ:: የተሰጠኝም ለእሥረኛ ልሰጥ ስለሆነ ለሚቀበለኝ እሰጣለሁ» አለኝ:: መቼም ወጥመድ ውስጥ ነው የገባሁት:: ገንዘቡን ተቀበልኩትና ወደ መንገድ ወጣሁ:: ከመቶ ሜትር የበለጠ አልተራመድኩም፣ ወዲያው የአውራጃው ጸሐፊ የተባለው ከጢሻ ውስጥ ወጥቶ ከፊቴ ድቅን አለብኝ።

ወዲያውም እኔን እያየ ሊያስደነግጠኝም እየሞከረ ይጮህ ጀመር:: «እስረኛ እያመለጠ ነው! ድረሱልኝ ኡኡ! እስረኛ አመለጠ! ያዙልኝ» እያለ ጩኸቱን አቀለጠው:: ይህ ሁሉ የሚሆነው በአፍታ ስለነበረ አንድ ነገር ለመናገር ምንም ጊዜ አልሰጠኝም:: ለመሸሽ መሞከር የሚቻል ቢሆንም እንኳ የበለጠ ነገርን እንደሚያባብስብኝ አውቃለሁ:: ወዲያው ሰዎች በድንገት ከየአቅጣጫው እየዘለሉ ወጡ:: ሰውየውም የበለጠ እርዳታ በመጠየቅ ተጨማሪ ሰው እንዲወጣ ይጮህ ነበር። እንደ አደገኛ ወንጀለኛ አድርገውም ከበቡኝ። አሥር ሆነው እያመለጡ ነበር በማለት እየጮኹ እኔን እየገፈተሩኝ ወደ አንድ የተከፈተ ቤት አስገቡኝ::

ይህ ሁሉ የሚሆነው ወደ ማታ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ነበር:: ቦርና የሚባል የአካባቢው ሰው ባንዲራ ሲያወርድ ጩኸት ሰምቶ ወደ ግርግሩ ቦታ እየተጣደፈ ደረሰ።

አሁን ደግሞ ያስያዘኝ የአውራጃው አስተዳደር ጸሐፊ ወደ ቤት ገባና በሩን በርግጫ ሲለው በሩ ተሰበረ:: ፈጥኖም ወደ ቤት ገባና ገፍትሮ የለበስኩትን ነጣ ያለ ኮት አወለቀብኝ:: ከላይ የለበስኩትን ሸማ ካነሣ በኋላ ሱሪዬን ለመቅደድ ሞከረ:: ይህ ሁሉ ሲሆን ሌሎች ሦስት ሰዎች በዱላ ይደበድቡኝ ነበር።



ዋና ጸሐፊው አሁንም እየገፈተረኝ ወደ ውጪ አወጣኝ:: በበሩ በኩል ገፍትሮ መንገድ ላይ ጣለኝ:: ከድብደባ ሊያድነኝ ይሁን ወይም ሰቅሎ ሊገድለኝ ነገሩ አልገባኝም።

እኔም፣ «አቤት! አቤት!» እያልኩ እጮህ ጀመር:: «እስረኛ ከሆንኩ፣ ለምን ትደበድቡኛላችሁ? የሠራሁት ወንጀል ካለም ምን እንደሆነ ንገሩኝ:: በአገሪቱ ሕግ መሠረት ፍርድ ቤት ቀርቤ መልስ ልሰጥ እችላለሁ:: እንዴት በዱላ ታስደበድቡኛላችሁ? አቤት! አቤት!» እያልኩኝ ጩኸቴን ቀጠልኩኝ።

ማንም ትኩረት ሰጥቶ አልሰማኝም:: መንገድ ተላላፊዎችም ወደ እኔ ሳይመለከቱ መንገዳቸውን ይቀጥሉ ነበር። ማንም ሰው እርዳታ ሊያደርግልኝ የሞከረ አልነበረም::

ለብቻዬ ተለይቼም ጮክ ብዬ፣ «እናንተ ካልሰማችሁኝ፣ እግዚአብሔር ይሰማኛል:: እግዚአብሔር ይረዳኛል:: አሁን እርሱ ይረዳኛል» አልኩኝ።

እስካሁን ማንነቴን ያስተዋለ አልነበረም:: አስቀድሞ ወደ ነበርኩበት ፖሊስ ጣቢያ ከመመለስ ይልቅ፣ እየገፈተሩኝ ከከተማ አልፎ ወደነበረው ቤት ወሰዱኝ:: ቦታው ለመድረስ ረዥምም ጉዞ ማድረግ ያስፈልግ ነበር:: መንገዱም ጎድጓዳ ሲሆን፣ ዝናብም ይዘንብ ነበር። ሰዎችም ሳያቋርጡ በመደብደብ ይረጋግጡኝም ነበር። ዝናቡ በቆርቆሮ ክዳን ላይ በኃይል ይዘንብ ነበር:: ጊዜውም እየጨለመ ሄደ:: በዚያ ፖሊስ ጣቢያ አንድ እሥረኛ ብቻ ይታይ ነበር:: ስሙም አሳ የሚባል ሲሆን፣ የታሠረውም በመግደል ወንጀል ነው። ዘበኛውም ግራ እጄን ከእሥረኛው ቀኝ እጅ ጋር አያይዞ በሰንሰለት አሠረኝ:: ሰውየው በእግር ብረት ታሥሮ ነበርና የእኔንም እግር በእግር ብረት አሠረኝ። በሁለታችንም እግር ብረት መካከል ትንሽ ክፍተት ብቻ ስለነበረው ለመራመድ አንችልም ነበር:: ሰውየው እንደ ሕፃን በእጆቹና በእግሮቹ ይሄድ ነበር:: የታሠርንበት ክፍልም በጣም የቆሸሸና በተባይ የተሞላ ነበር። በዚያን ጊዜ በቁንጫ፣ በቅማልና በትኋን መነከስ ለእሥረኞች ተጨማሪ ቅጣት ነበር። በቀድሞ ጊዜማ እሥረኞቹ የሚተኙበት ሣር ይሰጣቸው ነበር። በዚህ ክፍል ግን ከተጠራቀመ ቆሻሻ በስተቀር ምንም የለም። በመጨረሻ ግን እኔ በዙሪያው እየተሳብኩኝ ጥቂት ወረቀቶችንና የሰንበሌጥ ሣር አግኝቼ መደብ መሳይ ከፍታ ባለው ወለል ላይ ለማንጠፍ ቻልኩኝ:: በአጠቃላይ ለመኝታ የሚመች ባይሆንም፣ መቼም

ከምንም ቦታ ይሻል ነበር። እኔም በዚያ አቧራ ላይ እጋደም ነበር። በአቧራውም ውስጥ ከመሬት የፈለቁ እስኪመስሉ ድረስ እጅግ ብዙ ቁንጫዎች ነበሩ።

ማጅራቴን ያመኛል፣ ጀርባዬ ሰንበር አበጅቶ ያመኝ ነበር:: ሰዎቹ ጀርባዬን፣ ፊቴንና እግሮቼን በዱላ ቀጥቅጥ አድርገው ነበር የደበደቡኝ ። መቀመጫዬ ብዙ ሰንበር አበጅቶ ጠቁሯል። በጡጫና በዱላ ክንዶቼና መላው የሰውነቴ ክፍል ሁሉ በድብደባው ተጎድቷል:: ከዱላቸው የተረፈ የሰውነቴ ክፍል አልነበረም:: መላው አካላቴ አብጦ ያመኝ ነበር:: በመሃል ከተማ ሰዎቹ እየገፈታተሩ በወሰዱኝ ጊዜ ኃይለኛ ዝናብ ስለደበደበኝ ልብሴ እንዳለ ርሷል። ብርዱ እስከ አጥንቶቼ ዘልቆ ስለገባ ያንዘፈዝፈኝ ነበር:: የምቀይረው አንሶላ እንኳን ስላልነበረኝ የረጠበውን ሳላወልቅ ለመቆየት ተገደድኩኝ:: በሚቆረቁረው ቦታ ላይ እየተንቀጠቀጥኩ ተጋደምኩ:: ሥቃዬ ከመብዛቱ የተነሣ ተማርሬ ሞትን እመኝ ነበር። ቶሎ ብሞትና ከዚያ ሁሉ ሥቃይ ብገላገል እመርጥ ነበር።

ለመተኛት በፍጹም አልቻልኩም:: ጥቅልል ብዬ ተኝቼ ሙቀት ለማግኘት እጥር ነበር:: ወዲያው አንድ ሰው ከበር ቆሞ፣ «ማን ነህ?» ብሎ ጠየቀኝ።

## መልአክ ታየ

በድምጹ ወዲያው አወቅኩት፣ ሌላው ፖሊስ ነበር። «እኔ ነኝ፣ መሐሪ» አቃሰትኩኝ:: ሰውየውንም አስታወስኩት:: ልቤ ቀለጠ:: እንደማይረዳኝ እርግጠኛ ነበርኩ።

ፖሊስ ከመሆኑ በፊት ግብር ሰብሳቢ ነበር:: እንደ ሌሎቹ ከፍተኛና ዝቅተኛ ባለሥልጣኖች እርሱም በአቅሙ ትንሽ ንጉሥ ነበር። አንድ ቀን እኔ ለስብከት ሄጄ በነበርኩበት ወደ ቤቴ መጥቶ የምታርሰው መሬት ሕጋዊ ያልሆነ ነው ብሎ የቤቴን በር ሰብሮ በመግባት እቤት የነበረውን ዕቃ ሁሉ ወደ ውጪ በመወርወር ልጆቼን በማስፈራራት ሰብስቦ ለእርሱ እንዲሠሩለት ያስገድዳቸው ነበር።

ወደ ቤቴ ተመልሼ ይህ ሰው የሠራብኝን ሁሉ ላይ ክስ መሠረትኩበትና ታሠረ። ያን ሁሉ በደል ሊፈጽምብኝ የቻለው ያለ አንዳች ምክንያት እንደነበረም አስመሰከርኩበት። ከተቀጣም በኋላ



የወሰደውን ንብረቴን ሁሉ መለሰልኝ:: በኅብረተሰቡም መካከል አሳፍሬዋለሁ:: ታዲያ እንዴት ይረዳኛል ብዬ እጠብቀዋለሁ?

«አሃ አንተ ነህ ? እዚህ ምን ትሠራለህ? ምን ዓይነት መጥፎ ድርጊት ብትሠራ ነው እዚህ እስካሁን የቆየኸው?» አለኝ:: እኔም ከአነጋገሩ በመነሣት ከዚህ ሁሉ በኋላ ሊረዳኝ ይችላል ብዬም በራሴ አሰብኩ።

«ማንንም አልሰደብኩም:: የማንንም ንብረት አልሰረቅሁም:: የማንንም ሚስት አልደፈርኩም:: (በዚያን ጊዜ ከፍተኛ ወንጀል ተብለው የሚጠቀሱና ሰዎችን ለእሥር የሚዳርጉ ሦስት ከባድ ጥፋቶች እነዚህ ነበሩ።) ለእኔ ግን ይህ እሥራት የደረሰብኝ ወንጌላዊ በመሆኔ ብቻ ነው:: ዕርዳታውን እንዳልለምን ሕመምና ድካም እየተሰማኝ ስለነበረ አልቻልኩም:: ምን እንደተፈጸመብኝ ግን በአጭሩ አስረዳሁት።

የረጠበ ልብስ እንደ ለበስኩና በጣም እንደ በረደኝ ተመለከተኝ:: ምንም ነገር እንዳልዋሸ ሁለቱም ግልጽ ነበር። በከተማው ውስጥ ተከሥቶ የነበረውን ሁካታ (ረብሻ) ስለሰማ ክፉኛ እንደ ተደበደብኩ አውቋል:: ይህን ሁሉ ለእርሱ መንገር አስፈላጊ አልመሰለኝም ።

«ምን እንደማደርግ እስቲ አያለሁ» አለኝና ወደመጣበት ተመለሰ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ወፍራም ካፖርት ይዞ ተመለሰና በቀዳዳ እየገፋ አስገባልኝ። የግሉ ካፖርት እንደሆነም አወቅኩ:: በከፍተኛ ሁኔታ (ስሜት) አመሰገንኩት። ለራሴም ካፖርቱን ለበስኩኝ:: በወለሉ ላይ ተመልሼ ተጋደምኩኝ። ቀስ በቀስም እየተሻለኝ እንደሆነ አስተዋልኩኝ:: እየቆየሁ ስረዳም የተወረወርኩበት ክፍል ሰፊ እንደሆነ አየሁና ምናልባት ሌሎች ታሣሪዎችም ሊኖሩ ይችላሉ ብዬ ገመትኩ።

በትልቁ ክፍል የነበሩትን እሥረኞች ጫጫታ ቀሰቀሳቸው::

«መሐሪ፣ አንተ ነህ?» የሚል ጽምፅ ከጨለማው በኩል ጠራኝ::

«አዎን፣ እኔ ነኝ እዚህ ያለሁት» ብዬ በመጽናናት ስሜት ኩርምት ብዬ ተናገርኩ።

ለካስ የአቶ ሰለሞን ድምጽ ኖሯል:: ይህ ሰው በቁጫ በጣም ቃዋቂ የነበረ ሲሆን፣ ከባለሥልጣኖች ጋር በገንዘብ ጉዳይ ሳይስማማ በመቅረቱ ጉዳዩ እስኪጣራ ድረስ ወደ እሥር ቤት አስገብተውታል። ብዙ ሰዎች ፖሊስ ጣቢያውን ከመንግሥት ሆቴል የማይበልጥና የማያንስ አድርገው ገምተዋል። እዚያ መሆን መጥፎ የሆነ ማኅበራዊ ስም አያሰጥም::

ቦታው ሕዝባዊ ምሥጢር የሆነ ነው። ተቃዋሚህ ቀኙን ካገኘብህ በፖሊስ ጣቢያው ጥቂት ሌሊቶች ማሳለፍ ትችላለህ:: በሌላ መንገድ ደግሞ የበለጠ ተጽዕኖ ካሳደርክበት እርሱ እንዲታሠር ማድረግ ትችላለህ:: ይህ የጋራ የሆነ በየቡና ቤት የሚወራ ወሬ ነበር።

«ምን ሆነህ ነው እዚህ የገባኸው? አለና አቶ ሰለሞን ጠየቀኝ::

«አይ ምንም አይደለም»

«ስትሠርቅ ይዘውሃል ወይ?» አለኝ:: ስርቆት ያኔ በሁሉም ቦታ የተለመደ ነበር:: በስርቆት መያዝ ማለት ውርደት ብቻ ሳይሆን ደደብነትም ነው።

«አይደለም፣ ምንም አልሰረቅሁም» ብዬ በረዥሙ ተነፈስኩኝ::

«እሺ ስርቆ መያዝ ደደብነት መሆኑን ካወቅክ እዚህ ለምን እንደ ታሠርክ ንገረኝ:: አንተን እዚህ በማግኘቴ በጣም እደነቃለሁ:: ምን ሆነሃል? ለምንድን ነው እጅህን በሰንሰለት የታሰርከው? በእግረ ብረት አላሠሩህም፣ አሥረውሃል እንዴ?»

ጉዳዩን በዝርዝር ነገርኩት:: ወደ ጎሩ የመጣሁት ወንጌላዊ ሆኜ ነው:: ወንጌልን በመስበኬ ምክንያት እዚህ ለመታሠር በቅቻለሁ አልኩት:: «ለባለሥልጣኑ ጉቦ አልሰጥህም በማለቴም ተደብድቤአለሁ» ብዬ አስረዳሁት:: ወዲያውም፣ «ወታደር! ዘበኛ!» ብሎ ወደ ውጪ ተጣራ::

መልስ ሲያጣም፣ እየጮኸም በሥራ ላይ የነበሩትንም ዘበኞች መጣራት ጀመረ:: «ወታደር! ዘበኛ! የላችሁም እንዴ» እያለ ተጣራ።

በእንቅልፍ ላይ የነበረ ወታደር ወደ በሩ እየተራመደና እየተራገመ ለምን እንደቀሰቀሰው ለማወቅ ጠየቀው።

«ስማ አንተ! ቁልፍ አምጣና የዚህን ሰውዬ የእጅ ሰንሰለትና የእግር ብረት ፍታለት:: እርሱ የእኔ ወዳጅ ነው:: አደገኛ እሥረኛ አይደለምና ልቀቀው። በአንድ ደቂቃ ውስጥ የእጆቹን ሰንሰለትና የእግር ብረቱን ባትፈታለት፣ በእሥረኞች ላይ ሰብአዊነት የጎደለው ጭካኔ እንደፈጸምክ በመግለጽ በሕግ እከስሃለሁ» አለው።

ወታደሩ በማስፈራሪያው ባይደነቅም፣ «አንድ መልካም ነገር፣ ሌላ መልካም ነገረ ያስከትላል» እንደሚባለው ተረት አቶ ሰለሞን በጣም ሀብታም ሰው መሆኑን ያውቅ ነበርና አድርግ ያለውን ለማድረግ



ተስማማ። ወዲያው መክፈቻ ቁልፎች አመጣና የእጆቼን ሰንሰለትና የእግሮቼን እግር ብረት ፈታልኝ።

አቶ ሰለሞን ለራሱ ያስመጣው የዘንባባ ኬሻና ወፍራም የብርድ ልብስ ነበረው። አብሬው እንድተኛም ጎተጎተኝ:: በድካምና በተባዮች የተጎዳው ሰውነቴ በኬሻ የመተኛት ድሎት ከማግኘቱም በላይ፣ በወታደር ካፖርትና በወፍራም ብርድ ልብስ የበለጠ ሙቀት አገኘሁ:: ወዲያውም መልካም እንቅልፍ ተኛሁ።

በነጋታው በጣም የጤንነት ስሜት ተሰማኝ:: እንደወትሮዬም ፈገግታ ማሳየት ጀመርኩ:: ለጌታ ክብር ይህን ዓይነት ሥቃይ በመቀበሌም ደስታ ተሰማኝ:: ባለፉት ሌሊቶች የተቀበልኳቸው ጡጫና ጥፊ ዳግመኛ አይጎዳኝም:: የተኛሁበትም የአቧራ ወለል እንደ ሌላው አቧራ አልመሰለኝም። ደሜን ይመጥጡ የነበሩት ቁንጫዎችና ተባዮች ከሌሎቹ ተለይተው አልጎዱኝም:: በዚህ ዓይነት ሥቃይ የወንጌል መስካሪ በመሆኔ በጣም ደስ አለኝ:: ከአቶ ሰለሞንም ጋር ሦስት ቀን ለመቆየት ችያለሁ።

ካፖርቱን ሰጥቶኝ የሄደው ውቤ የተባለ ወታደር እንደገና ሊረዳኝ ተመልሶ መጣ:: እንዴት ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት እንደ ተፈጸመብኝ አይቶ ስለነበር ወደ ሦስት የመንግሥት ቢሮዎች ማመልከቻዎችን ጽፎልኛል:: የካርቦን ግልባጩን ለእኔ ከተወልኝ ጋር በጠቅላላ ስድስት ገጽ ወረቀት ጽፎአል ማለት ነው:: ማመልከቻዎቹን ራሴ እንዳቀርብ አምጥቶ ከሰጠኝ በኋላ፣ አንዳንድ ጓደኞቹን ለማን መስጠት እንደሚገባኝ እንዲጠቁሙኝና እንዲረዱኝ አሳሰባቸው። ማመልከቻዎቼን ባቀረብኩኝ ጊዜም ከእያንዳንዱ ቢሮ ስለመቀበላቸው ደረሰኝ ሰጥተውኛል።

## የውጪ አገር ሚስዮናውያን ወደ ጎሩ ተመለሱ

በዚያን ጊዜ ሚስተር ዶናልድ ግሬይ፣ ሚስተር ቢል ካርተርና ሚስተር ዲክ ማክሊላን የሚባሉ ሚስዮናውያን በባኮ የኤስ ላይ ኤም ጣቢያ ለመክፈት ሲሄዱ በጎሩ በኩል ያልፉ ነበር። ሚስተር ግሬይ ወደ ተወሰኑ የመንግሥት ቢሮዎች ማመልከቻዬን ለማቅረብ ስሄድ አብረውኝ ሄደዋል:: ለጊዜው ግን በማመልከቻዎቼ በኩል ያደረግነው ጥረት ስኬታማ አልሆነልንም ነበር::

ከትንሽ ጊዜ በኋላ በባኮ ከሚስተር ግሬይና ባለቤታቸው ጋር አጭር ቆይታ አድርጌአለሁ። ያኔ የመንግሥት ቢሮዎች በሙሉ በባኮ የነበሩ ሲሆን፣ ሚስተር ዲክ ማክሊላን ቤቶችን በመገንባት እነሚስተር ግሬይን ይረዱአቸው ነበር። ቆየት ብለው ወደ ጂንካ ከተማ ተዛውረዋል። የመንግሥት ቢሮዎች ለሚስዮኑ ጣቢያ ቅርብ ነበሩና በምንሄድበት ጊዜ በቅርብ እየተከታተሉንና ሰበብ እየፈለጉ ያሥሩን ነበር። በአንድ ወቅት በባኮ እሥር ቤት ታሥረን በነበረ ጊዜ ሚስተር ማክሊላን መጥተው አስፈትተውናል:: የመንግሥት ባለሥልጣኖችም ከሚስዮናውያን ጋር ግንኙነት እንዳለን ሲረዱ በእስር ቤት ሊያቆዩን አልፈለጉም:: ነገር ግን ስብከታችንን ለማደናቀፍ የሚቻላቸውን ከማድረግ አልተቆጠቡም ነበር።

እኔ ግን በሥራዬ ወደ ፊት እገሰግስ ነበር:: በቡልቂ ፖሊስ ጣቢያ በነበርኩኝ ጊዜ አየለ የሚባል ሰው ወደ እኔ መጥቶ፤ «እነዚህ የውጪ ዜጎች የሚረዱህ ለምንድን ነው? ምን እንዲያደርጉልህ ነው የምትፈልገው? አስቀድሞ የደበደቡህን ሰዎች በእነርሱ ልታስደበድብ ነው? እነርሱስ እዚህ ምን ይሠራሉ?» ብሎ ጠየቀኝ::

እኔም፣ «እኔን ለመረዳት አልመጡም፤ ነገር ግን ወደ ባኮ እየሄዱ ናቸው:: እንዲያውም ከማናቸውም ጋር ከዚህ ቀደም አልተገናኘሁም» አልኩት። «እዚህ የቆዩበት ምክንያት መንገድ የሚመራቸውንና ዕቃ የሚሸከምላቸውን ሰው ፈልገው ነው» ብዬ አረጋገጥኩለት።

ሚስዮናውያኑ በከተማ አርፈው በነበሩበት ወቅት እኔም እዚያው ታሥሬ ነበር:: ያኔ ሚስተር ማክሊላን ገና ያላገባ ወጣት ነበር:: እርሱም በእስር ቤት መጥቶ የጎበኘኝ ሲሆን፣ በዱላ የተደበደብኩበትን አካሌን በሙሉ እየደባበሰ አይቶኛል፣ ምግብም ሰጥቶኝ ተመልሷል።

በመጨረሻም ሦስቱም መንገድ የሚመራቸውንና ዕቃቸውን የሚሸከሙላቸውን ሰዎች አግኝተው ወደ ባኮ አምርተዋል። ለተወሰነ ጊዜ ማናቸውንም አላየሁም፤ አልተገናኘሁምም:: በደቡባዊ ጎፋ በድንገት የተገናኘሁአቸው ወንጌልን የመሰከርኩላቸው የአሪ ሕዝብ ናቸው። ሚስዮናውያኑ ከቡልቂ ከተማ እንደ ወጡ ማንም የሚረዳኝ አልነበረም።

በዚህ ፖሊስ ጣቢያ እሥራ ዘጠኝ ቀን አቆይተውኝ ወደ ቀድሞው ፖሊስ ጣቢያ መለሱኝ። ባለሥልጣኖቹም የደረሰብኝን በደል ሁሉ ሳያውቁ ነው ያደረሱብኝ ብለህ ፈርም ብለው አስገደዱኝ። ይህን



የሚያደርጉት ላደረሱብኝ በደል እንዳልከሳቸው አስቀድመው ዘዴ መፍጠራቸው ነበርና አልፈርምም አልኳቸው።

የአውራጃው ጸሐፊ ያን ሁሉ ችግር ያነሣሣብኝ ታሥሮ ወህኒ ቤት መግባቱን ሰማሁ:: እርሱ ብዙ የሚግባቡ ጓደኞች ስላሉት በግሌ ከስሼው ምንም እንደማላደርገው አውቅ ነበር።

አንድ ቀን ሁለት ሽማግሌዎች ልኮ፣ «እንታረቅ» አለኝ::

«ምን ላድርግ?» ብዬ ራሴን ጠየቅኩኝ:: እንዴት ከእርሱ ጋር ለመታረቅና ሰላም ለመፍጠር እችላለሁ:: ደብድቦኛል:: በእርግጥ ከልቤ ይቅርታ አድርጌለታለሁ?» ነገር ግን ወንጌላዊ እንደ መሆኔ ከእርሱ የካሳ ገንዘብ ተቀብዬ መታረቅ ስሕተት እንደሆነ አስተዋልኩ:: ስለዚህ ከእርሱ ጋር አልታረቅም ለማለት አልቻልኩም።

ግራ ተጋባሁ:: ለሽማግሌዎቹ ምን ብዬ እንደምመልስላቸው አላውቅኩም ነበር:: በእኛ አገር አንድ አባባል አለ፣ «አዞ በውኃ ውስጥ ተቀምጦ ጆሮውን ያጥመለምላል» ይባላል:: ይህም ማለት አዞው ውኃውን እያንቦጫረቀና የማይጎዳ እየመሰለ በውስጡ ታዋቂ ቋንቋ ግን አዞው ሊበላህ ነው እንደ ማለት ይቆጠራል። ይህ ከጥቂት ሳምንታት በፊት ያጠቃኝ «አዞ» አሁንም ሊያጠቃኝ ይሆን?

ሌላው ችግር ደግሞ ማመልከቻ ጽፎልኝ የነበረው ሰውዬም ወደ ሌላ ስፍራ ተዛውሯል:: ያንን ማመልከቻ በመስጠት የረዱኝ ሚስዮናውያንም ከዚያ ለቅቀው ሄደዋል:: ፈቃድ ተቀብዬ ማመልከቻዬን ምን እንዳደረጉ ለመጠየቅ ወደየቢሮዎቹ ሄድኩኝ:: የሰጡኝን ደረሰኝ ባሳያቸውም እንኳን፣ ማመልከቻዬን ወዴት እንዳደረሱት አያውቁም። «ለጊዜው የት እንዳስቀመጥነው አጣን» የሚል መልስ ሰጡኝ። ያ ማለት ምን ማለታቸው እንደሆነ ገብቶኛል:: ከደበቁበት ቦታ ሊያስገኝ የሚችለው ጉቦ ብቻ ነው:: እኔም፣ «እባካችሁ ይሄ ሰው ጠላት የሆነብኝ ሊገድለኝ እየሞከረ ነው:: ነገር ግን ወንጀለኛ አለመሆኔን ለመግለጽ መብት አለኝ :: ቢያንስ ይህ መብት እንዳለኝ አሳስባለሁ።» አልኳቸው::

«አሁን ምን ማድረግ አለብኝ?» ብዬ ራሴን ጠየቅኩኝ:: በጣም ተጨነቅኩና ተረበሽኩ:: ምን ማድረግ እንደነበረብኝ አላውቅም:: ማንም ሊረዳኝ የሚፈልግ አልነበረም። እኔም የሚረዳኝ ሰው ባለመኖሩ ትንሽ ጊዜ ልቆይና እስቲ የሚሆነውን ልይ ብዬ ወሰንኩኝ:: ወደ እኔ ተልከው ለመጡት ሽማግሌዎች መልስ መስጠትም ይኖርብኛል። ስለዚህ

መልስ ከመስጠቴ በፊት ላስብበት እስቲ የአንድ ሳምንት ጊዜ ስጡኝ አልኳቸው::

ሽማግሌዎቹም፣ «ከስምንት ቀን በኋላ እንመለሳለን» ብለው ወደመጡበት ተመለሱ::

አሁን ለሽማግሌዎቹ ጥያቄ ከመስማማት በስተቀር ሌላ ምርጫ የሌለኝ ይመስለኛል። ይህ የታሠረው የአውራጃው አስተዳደር ጸሐፊ ብዙ ወዳጆች እንዳሉት አውቃለሁ:: ያለ ሌላ ድጋፍ ከእነርሱ ጋር መጣላት አልችልም። «እሺ ይሁን፣ ከዚህ ከደበደበኝ ሰው ጋር እታረቃለሁ:: ቀን ቅጠሩና ተጨባብጠን እንስማማለን» አልኳቸው::

ይህም ማለት ዳግመኛ ምንም ክስ አልመሠረትበትም ማለት ነው።

የቀጠሮአችን ቀን ከመድረሱ በፊት ያ ባለሥልጣን አውልቆ የቀደደብኝን ኮቴን አንድ ሰው ይዞ ሲመጣ፣ ሌላኛው ደግሞ በግርግሩ ወቅት የተወሰደብኝን ቀበቶዬን ያለ ዘለበት ይዞ መጣ:: ያ ሁሉ ለእኔ ምሥጢር ነበር:: ምን ይካሄድ እንደነበር ሊገባኝ አልቻለም:: ከጀርባዬ እየቀደዱ አውልቀው የወሰዱብኝን ሸሚዜን ግን አልመለሱልኝም።

የሚያስደንቀው ነገር ቢኖር ለካስ ለደረሰብኝ ድብደባና በደል ፍርድ ቤት ሕጋዊ እርምጃ እየወሰደበት ስለነበር ፀጉሩ ተላጭቶ ወደ ትልቁ ወህኒ እንዲገባ ተደርጓል:: ሌላው ደግሞ ለዚያ ብጥብጥና ሁከት ምክንያት እኔ ስለሆንኩኝ ከጎፋ በግዳጅ ወደ ቁጫ እንድመለስ ወስኖብኛል።

ይህን የተፈረደብኝን ፍርድ በሰማሁ ጊዜ፣ «ፍርድ ቤት የወሰነብኝ ውሳኔ የባሰ አስከፊ ነው» ብዬ ገመትኩ::

ለራሴም ብቻ አይደለም፣ «ለምን ከዚህ ወጥቼ ሌላ ቦታ እንድሄድ እገደዳለሁ?» በማለት የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመቃወም አመለከትኩ።

ዳኛውም ማመልከቻዬን ተቀበሉና ለሚቀጥለው ዓርብ ቀጠሩኝ:: ያንን ዓርብ መጠበቅ የሞት ቀጠሮ የምጠብቅ መስሎ ታየኝ:: በቀጠሮው ቀን ቀርቤ ምን  እንደምናገር አላውቅም ነበር።



## በተአምር መፈታት

በ1942 ዓ.ም አካባቢ በብዕር መፈረም የማይችሉ ሰዎች በአውራ ጣታቸው ላይ ቀለም ተቀብቶ በወረቀት ላይ እንዲፈርሙ ይደረግ ነበር። በቀጠሮአችን ቀን ዓርብ ዳኛው ዳግመኛ በጎፋ እንዳልሰብክ በጣቴ የሚያስፈርሙኝ ወይም በብዕር የሚያስፈርሙኝ መስሎኝ ነበር:: ያን ማድረግ በፍጹም የማይታሰብ ነው። እግዚአብሔር ሊገድለኝ ከፈለገ፣ ያ ሌላ ጉዳይ ነው። ሞቼም ሰዎች ሬሳዬን ወደ ቁጫ ተሸክመው በመውሰድ የሚቀብሩኝ ከሆነ መልካም ነው:: ግን እንዴት እግዚአብሔር አድርግ ያለኝን ለመሰረዝ በፊርማዬ አረጋግጣለሁ? በማለት እንዲህ ብዬም ጸለይኩ።

«ጌታ ሆይ፣ የሚሉኝን እንደማላደርግ ታውቃለህ:: ይህ ዓርብ እንዳይመጣ አድርግ:: የቀጠሮው ቀን እንደ አንድ ዓመት ይርዘም:: ለአንድ ዓመት ያህል በእስር ቤት መክረም ለእኔ ምንም አይደለም:: እኔ በወረቀታቸው ላይ በምንም ዓይነት መፈረም አልፈልግም» አልኩኝና ጸለይኩ።

በዚያ ሳምንት ውስጥ የመጣብኝ ትእዛዝና የተከናወነ ነገር አልነበረም:: በመጨረሻም ያ ዓርብ ደረሰ:: እኔ ግን በፍጹም ደስተኛ አልነበርኩም:: እግዚአብሔር ለምን አንድ ነገር አላደረገም? ወደ ወህኒ ብገባ ምንም አይደለም:: የደረሰብኝንም ድብደባ በዝምታ ችዬ ተቀብያለሁ:: የማልቀበለው ነገር ቢኖር በፈቃደኝነት ከጎፋ ወደ ቁጫ እመለሳለሁ ብዬ መፈረምን ነው:: እነርሱ ራሳቸው ቢያስገድዱኝና እንድወጣ ቢያዙኝ ያ ሌላ ጉዳይ ነው:: የሚፈልጉት ግን በፍቃዴ ተስማምቼ እንደፈረምኩ ሊያደርጉ ነው::

ስለዚህም በዚያ ዓርብ ጠዋት በሰፊው የወህኒ ቤቱ ክፍል አዝኜ በአግዳሚ ወንበር ላይ ተቀምጬ ነበር። ከፍርድ ቤት በማንኛውም ጊዜ መልእክተኛ መጥቶ ስሜን ይጠራል እያልኩኝ እጠብቅ ነበር:: ምን እንደምናገርም አላውቅም ነበር።

ወዲያውም ጀምበሩ የሚባል ወታደር እየተጣደፈ መጥቶ፣ «መሐሪ፣ መሐሪ፣ የማቴዎስ አባት! ፈጥነህ ውጣ እየተፈለግክ ነው:: ተጠርተሃል ሲለኝ፣ «ማን ነው የፈለገኝ» ብዬ በመገረም ጠየቅኩት። ብዙ ሰው የሚጠራኝ ሰው እንዳልሆንኩ አውቃለሁ:: ወታደሩም ኮሎኔል ይጠሩሃል አለኝ::

«ለምንድን ነው የሚጠሩኝ? ምን ይፈልጋሉ?» ብዬ ወታደሩን ጠየቅኩት::

«ሂድና ተገናኛቸው:: እኔ ምን አውቃለሁ?» አለኝ።

እኔም ወደ ኮሎኔሉ ቢሮ ገባሁና በስሜ ጠሩኝ::

እኔም፣ «አቤት ጌታዬ» ብዬ መለስኩኝ::

«ልብስህን ይዘህ ሂድ» ብለው አዘዙኝ:: እኔ ሕልም የማይ ነበር የመሰለኝ::

«ጌታዬ፣ የት እንድሄድ ይፈልጋሉ?» አልኳቸው::

«ውጣ! ወደ ቤት ሂድ!» አሉና ጮኹብኝ::

«ወደ የትኛው ቤት ልሂድ ጌታዬ?» አልኳቸው::

«ምን ማለትህ ነው? ወደ ራስህ ቤት ነዋ! ቤት የለህም እንዴ?» አሉኝ::

«አይሆንም፣ ጌታዬ» አልኳቸው::

«እውነትህን ነው? የምትሄድበት ቦታ የለህም?» አሉኝ።

ውይይታችን እውነት መሆኑን አላመንኩም ነበር:: ፀጉሬ ተላጭቷል፣ የለበስኩትም ቁራጭ ጨርቅ ነው። ለአያሌ ወራት በዚህ በትልቁ ወህኒ ታሥሬ ቆይቻለሁ:: ጎፋን ለቅቄ ዳግም ላለመመለስ ወደ ቂሜ እንድመለስ ያስፈርሙኛል ብዬ እጠብቅ ነበረ። ኮሎኔሉ ፊት ለፊቴ በእርግጥ ተቀምጠው ነው ያሉት:: ልብስህን ወደ ቤትህ ይዘህ ሂድ የሚሉኝ እውነት ነው? ይህ ሕልም ነው:: እውነት ሊሆን አይችልም::

«ቤት የለህም? ለምን ወደ ራስህ ቤት አትሄድም?» ብለው ደግመው ጠየቁኝ ኮሎኔሉ።

«የማን ቤት?» ብዬ እንደገና ጠየቅኳቸው::

«የራስህ ቤት» አሉኝ::

«እኔ ቤት የለኝም» አልኳቸው:: ወዲያው የምንነጋገረው በሕልም አለመሆኑን አስተዋልኩኝ:: ወዲያው በር ተከፈተና ስሜ በላዩ የተጻፈበት ልብሴ በጠረጴዛ ላይ ከፊቴ ተቀመጠልኝ::

«እሺ» አልኩና በትልቁ መዝገብ ላይ ፈረምኩኝ:: ልብሶቼንም እንሥቼ ዝቅ ብዬ እጅ ከነሣሁአቸው በኋላ የኮሎኔሉን እጅ ጨብጬ ከበሩ ወጣሁና መንገዴን ቀጠልኩኝ።

ማንም ጥያቄ ያነሣብኝ አልነበረም። ያሳዘነኝ ነገር ቢኖር የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አዘጋጅቼ እስረኞችን አስተምርበት የነበረ ማስታወሻዬን በትልቁ ወህኒ ቤት ጥዬ መሄዴ ነበር። በራሴ ኃላፊነት ዳግመኛ ወደ ወህኒ ቤት ለመመለስና ለመፈለግ አልደፈርኩምና ትቼ ሄድኩኝ።

አሁን ወደፈለግኩበት ለመዘዋወር ሙሉ ነጻነት አገኘሁ:: መስበኬንና ማስተማሬንም ጀመርኩ። ነገር ግን በደረቴ ውስጥ



የሚሰማኝ ሕመም እየባሰብኝ ሄደ:: በፍጥነት ወደ ሐኪም ቤት ሄጄ መታየት እንደሚገባኝም ተረዳሁ::

በዚህን ጊዜ አምቦ በሚባለው ቦታ የጥምቀት ሥነ ሥርዓት የሚካሄድበት ዕቅድ ነበረን። የተጠመቁት ሰዎች ሁሉም ስለ እምነታቸውና ባህርያቸው በሽማግሌዎች ተጠይቀዋል:: ከጥምቀቱ ሥነ ሥርዓት በኋላ ቄሶች መጥተው ለማጥመቅ ፍቃድ የላችሁም ብለውም ከሰውናል። ስለ ጥምቀት በምንጠየቅበት ቦታ ሁሉ መልሳችን፣ «አስተምረን እናጠምቅ ዘንድ ጌታ ኢየሱስ ተናግሮናል፤ በስሙና በሥልጣኑም እናጠምቅ ዘንድ የእርሱ ትእዛዝ አለን» የሚል ነበር።

ወንጌላውያን ጥምቀትን ስለሚያካሂዱ በተደጋጋሚ ይጠየቁና ይታሠሩ ነበር። በእርግጥ ስለተቃወሙ ማድረግ የምንችለው ትንሹን ነው::